መቐለ ዩኒቨርሲቲ

የህብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል (አማርኛ)

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በ2015 ዓ.ም በተዘጋጀው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሓፍ የቀረቡ ምንባቦች ተገቢነት ግምገማ

በሓጎስ ስብሃቱ

አማካሪዎች

ዶ/ር.ተ/ሃይማኖት ገ/ፃድቅ (phd)

አቶ አብርሃ ፀጋይ (MA)

ጥቅምት 2018 ዓ.ም

መቐለ

በ2015 ዓ.ም በተዘጋጀው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሓፍ
የቀረቡ ምንባቦች ተገቢነት ግምገማ

መቐለ ዩኒቨርሲቲ

የህብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል (አማርኛ)

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ
የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

በሓጎስ ስብሃቱ

አማካሪዎች

ዶ/ር ተክለሃይማኖት ገብረፃዲቅ (phd)

አቶ አብርሃ ፀጋይ (MA)

ጥቅምት 2018ዓ.ም

መቐለ

የህብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል (አማርኛ)

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

‹‹ ይህ ጥናት በ2015 ዓ.ም በተዘጋጀው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሓፍ የቀረቡ ምንባቦች ተገቢነት ግምገማ››በሚል ርዕስ በሓጎስ ስብሃቱ የቀረበ ነው፡፡ ጥናቱ፣ በተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ኤም.ኤ. ድግሪ ማሟያ የተሰራ በመሆኑ በውጭና በውስጥ ፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም----------ፊርማ----------ቀን----------

የውጭ ፈታኝ ስም----------ፊርማ----------ቀን----------

የውስጥ ፈታኝ ስም----------ፊርማ----------ቀን----------

ማረጋገጫ

‹‹ይህ ጥናት በ2015 ዓ.ም በተዘጋጀው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሓፍ የቀረቡ ምንባቦች ተገቢነት ግምገማ›› በሚል ርዕስ በመቐለ ዩኒቨርስቲ በህብረተሰብ ሳይንስ እና ቋንቋዎች ኮሌጅ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል በተግባራዊ ሥነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ.ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ስለሆነም አጥኚው ጥናቱን ሲሰራ ከተለያዩ ዋቢዎች ሃሳብ ወሰዷል፡፡ ምንጮቹንም በትክክለኛ የዋቢ አጠቃቀስ ያስቀመጥኩ መሆኔን እየገለፅኩ የጥናቱ ስራ ህጋዊ ባለቤት መቐለ ዩኒቨርስቲመሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ሓጎስ ስብሃቱ ዳንፋ

ፊርማ----------

ቀን----------

ምስጋና

ከጥናቱ ጅማሮ እስከዚህ ዕለት ላደረሰኝ ለልዑል እግዚአብሄር ምስጋናየን በእጅጉ አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠል ለስራየ ስኬት ትልቅ ድርሻ ከነበራቸውን ወሳኝ ሰዎች፣ ለጥናቴ ስራ ሞያዊ አስተያየት በመስጠት ላገዙኝ፣ ላረሙና ላስተካከሉ አማካሪዎቼ ለዶ/ር ተ/ሃይማኖት ገብረፃድቅ እና ለአቶ አብርሃ ፀጋይ ከአክብሮት ጋር ምስጋናየ የላቅ ነው፡፡ ለእኔ የሞራል ስንቅ፣ የድካሜ ብርታት የሚሆን ምክርን ከጎኔ ሆና ለሰጠችኝ፣ ላበረታታችኝ ውድ ባለቤቴ መድህን ሃጎስ ምስጋናየ በእጅጉ ይድረስሽ፡፡ ለጥናቴ ስራ ድርሻ ለነበረው ለመቐለ ዩኒቨርስቲና ለጥናቴ መረጃ በመስጠት ቀና ትብብራቸውን ለሰጡኝ መምህራን ለስራየ ስኬት የእናንተም ድርሻ አለበትና ምስጋናዬን ይድረሳችሁ፡፡

አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2015 ዓ.ም በታተመው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ምንባቦች ተገቢነት መፈተሽ ነው። ጥናቱ አይነታዊ የምርምር አቅጣጫን የተከተለ ነው፡፡ የጥናቱ ንድፍ ደግሞ በገላጭ ጥናት (Descriptive Research) የቀረበ ነው፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ ለተመረጠው የክፍል ደረጃ የቀረቡት ምንባቦች ተገቢ መሆን አለመሆናቸውን የፈተሸ ስለሆነ ነው፡፡ ይህን ጥናት ለመስራት ከላይ በተጠቀሰዉ መፅሃፍ ዉስጥ የቀረቡት አስር ምንባቦች የጥናቱ አካላይ ሆነዋል፡፡ የጥናቱን መረጃዎች ለመሰብሰብ የሰነድ ፍተሻና ቃለ መጠይቅ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በእነዚህ መሳሪያዎች የተገኙት አይነታዊ መረጃዎች በገላጭ ተንታኝ ስልት እንዲተነተኑ ተድርጓል፡፡ ከጥናቱ ተተካሪ ምንባቦች ተገቢ መሆናቸዉን የተገመገሙት በGuba and Lincoln (1989)፣ በKramsch (1993)፣ በTaylor (2004)፣ በCummins (2017)፣ በArias (2007)፣ በWilliam (2004)፣ በStrunk and white (1959) እና በJoseph (1990) መስፈርቶች መሰረት ነው፡፡ የምንባቦቹም ሃሳብ ከወቅቱ ተጨባጭ ሁነት ጋር የተገናዘቡ፣ ባህላዊ ጉዳዮችን የሚገልፁ፣ መደበኛ የቃላት አጠቃቀምን የተጠቀሙ፣ የክፍል ደረጃው ተማሪዎች አንብበው የሚረዷቸው መሆናቸው፣ በበርካታ ውስብስብ አረፍተ ነገሮች የቀረቡ አለመሆናቸው፣ ግልፅና ቀላል ሃሳብ የያዙ መሆናቸውን በመፈተሽ ነው፡፡ በውጤቱም በሁሉም ምዕራፎች የሚገኙት አስሩም ምንባቦች ከወቅቱ ተጨባጭ ሁነት ጋር የተያያዙ እንደሆኑ፣ በምዕራፍ6፣ በምዕራፍ8 እና በምዕራፍ 10 ስር የሚገኙት ምንባቦች የኢመደበኛ ቃላት አጠቃቀም ችግር እንደሌለባቸው፣ በምዕራፍ7 እና በምዕራፍ9 የቀረቡት ምንባቦች ከባድ ሃሳብ የያዙ እንደሆኑ፣ ለክብደቱም መንስኤ የዘየ፣ የሙያ፣ ከባድና የፈሊጣዊ ቃላት መብዛት እንደሆኑ፣ በምዕራፍ1 እና በምዕራፍ9 ስር የቀረቡት ምንባቦች በበርካታ ውስብስብ አረፍተ ነገሮች እንደቀረቡ፣ መማሪያ መፅሃፉ ውስጥ የቀረቡት ሁለት ምንባቦች ከተማሪዎቹ አቅም አኳያ የሃሳብ ክብደት እንዳላቸው፣ የቀሩት ስምንት ምንባቦች ግን ለመረዳት ቀላልና ተገቢ እንደሆኑ ከሰነድ ፍተሻውና ከቃለመጠይቁ መረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለሆነም በመማሪያ መፅሃፍት ውስጥ የታዩት ጥሩ ጎኖች በመፅሃፍት አዘጋጆች በኩል ተጠናክረው ቢቀጥሉ ለክፍል ደረጃው ተማሪዎች ተገቢ ምንባቦችን ለማቅረብ መልካም ነው፡፡ የሚታዩ ክፍተቶችን ደግሞ የመፅሃፍት አዘጋጆች እንደግብዓት ቢጠቀሙበት፣ ተመራማሪዎች መነሻ ሃሳብ ቢያደርጉት ውጤታማ አድራጊ ምንባቦችን ለማሳናዳት አጋዥ ሃሳብ ይሰጣል፡፡

ይዘት ገፅ

ማረጋገጫ..... iii
ምስጋና iv
አጠቃሎ v
ምዕራፍ አንድ፤መግቢያ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 3
1.3.የጥናቱ ዓላማዎች 5
1.3.1 አጠቃላይ ዓላማ 5
1.3.2.ዝርዝር ዓላማዎች 5
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ 5
1.5 የጥናቱ ወሰን 6
1.6 የጥናቱ ውስንነት 6
ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት 7
2.1. የንድፈ ሀሳባዊ ፅሑፎች ክለሳ 7
2.1.1. የመማሪያ መጻሕፍት ምንነት 7
2.1.2 የምንባብ ተገቢነት 8
2.1. 3 በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የምንባብ አመራረጥ መስፈርቶች 8
2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 16
ምዕራፍ ሶስት፤የአጠናን ዘዴ 19
3.1 የጥናቱ ንድፍ 19
3.2 የናሙና አመራረጥ 19
3.2.1 የክፍል ደረጃ ኣመራረጥ 19
3.2.2 የትምህርት ቤት የናሙና አመራረጥ 19
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳርያዎች 20
3.3.1 የሰነድ ፍተሻ 20
3.3.2 ቃለ መጠይቅ 20
3.4 የመረጃ ኣሰባሰብና አደረጃጀት 21
3.5 የመረጃ ኣተናተን ዘዴ 21
ምዕራፍ አራት፡- የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ 22

4.1 የተጠኘው ሰነድ አጭር ቅኝት 22
4.2 የጥናቱ የመረጃ ትንተና 22
4.2.1 ከሰንድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች 24
4.2.2 ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች 33
4.3. የጥናቱ የውጤት ማብራሪያ 38
ምዕራፍ አምስት፡-ማጠቃለያ መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳብ 41
5.1 ማጠቃለያ 41
5.2 መደምደሚያ 42
5.3 አስተያየት 43
ዋቢዎች 44
አባሪዎች 48
አባሪ ‹ሀ› ለመምህራን የሚቀርብ የቃለ-መጠይቅ ጥያቄዎች 48
አባሪ ‹ለ›በቃለ መጠይቅ የተመረጡ የመምህራን ዳራዊ መረጃ 49
አባሪ. ‹ሐ› በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች መረጃ 49
አባሪ ‹መ› አማርኛ ቋንቋ ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ የቃለ-መጠይቅ ምልልሶች ቅጅ 50

ምዕራፍ አንድ፤መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ

በማንኛውም የትምህርት ሥርዓት ውስጥ የተማሪ መማሪያ መፅሐፍ የመርሃ ትምህርቱ ዋነኛ መተግበሪያ መሣሪያ ሲሆን፣ የክፍል ውስጥ ትምህርትን ይዘትና ባህሪ የሚቀረፅበት ነው (Cunningsworth፣1995)። እንደGrant (1987) ገለፃ ደግሞ መማሪያ መፅሓፍ የተማሪውን የትምህርት ደረጃ፣ፍላጎት፣ ዕድሜ የትምህርት ዓላማዎች መተግበሪያ የሚሆን ተመጣጣኝ፣ ተለጣጣቂና ተደጋጋፊ ይዘቶችን በውስጡ አደራጅቶ የያዘ ለማስተማሪያነት የሚያገለግል መሣሪያ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ የቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ በርካታ የትምህርት ይዘቶች የሚቀርብበት ሲሆን ምንባቦች አንዱ የይዘቱ አካል ናቸው፡፡ ምንባቦች የቋንቋ ግብዓት ምንጭ ከመሆናቸውም በላይ፣ አዳዲስ ቃላትንና ሰዋስውን ለመማር ያስችላሉ፡፡ ለተማሪዎች የጽሑፍ ሥራዎችም እንደሞዴል ያገለግላሉ። ከሁሉም በላይ እነዚህ ጽሑፎች ተማሪዎችን ከባህላዊ እሴቶች፣ ከተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችና ከአዳዲስ የአስተሳሰብ መንገዶች ጋር ያስተዋውቃሉ። ስለዚህ በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች ለተዘጋጁበት የክፍል ደረጃ ተገቢነት ያላቸው መሆን ይገባል፡፡

እንደ Richards & Schimdt (2002) ገለፃ የምንባብ ተገቢነት ሲባል ምንም እንኳን ሰፊ ትርጉም ቢኖረውም በመማር ማስተማር ሂደት አንድን የተመረጠ ርእስ ተማሪዎች እንዲለማመዱ የተፈለገው የንባብ ክሂል ለማለማመድ የሚኖረው ብቃት ነው፡፡ የምንባብ ተገቢነት የሚረጋገጠውም አንድ የተመረጠ ምንባብ የተፈለገውን ዓላማ ከግብ የሚያደርስ ሲሆን፣ መፅሃፉ ሲዘጋጅ እንደ ዓላማ ኣንግቧቸው የተነሳባቸውን ጉዳዮች ተማሪዎች በምንባቦች ተምረው ሲያሳኩ ነው።

በመማሪያ መጽሓፍ ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች ለተማሪዎች የማንበብ ክሂል መዳበር ትልቅ አስተዋፅኦ አላቸው። ምንባቦቹ ተማሪዎች የንባብ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ የሚያስችሉና ለማንበብ የሚያነሳሱ ሲሆኑ ተገቢነት እንደሚኖራቸው Grant (1987) ይገልፃል፡፡ ምንባቦቹ፣ የተማሪዎቹን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገቡ ከሆነ ተማሪዎች ምንባቦቹን ሊወዷቸው ይችላሉ። ከዚህም አልፎ የማንበብ ፍላጎታቸውም ሊጨምርና የማንበብ ክሂላቸው ሊዳብር ይችላል።

ነገር ግን ምንባቦቹ የተማሪዎቹን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያላስገቡ ከሆነ ተማሪዎች ምንባቦቹን ሊጠሉና የማንበብ ፍላጎታቸው ሊቀንስ ይችላል። በዚህ የተነሳ የማንበብ ክሂላቸው እንዳይዳብር ሊያደርጉ ይችላል። በመሆኑም በመማሪያ መፅሓፍ ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች ለተማሪዎች የማንበብ ክሂል መዳበር ትልቅ ፋይዳ ስላላቸው ምንባቦቹ ተገቢነትን የተላበሱ መሆን እንዳለባቸው Grant (1987) እና Lazar (2009 ይገልፃሉ፡፡ ይህ ጥናትም በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ባላቸው ተገቢነት ላይ ትኩረቱን አድርጓል፡፡

በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቋንቋ ክሂሎችንና የእውቀት ዘርፎችን ለማስተማር የሚቀርቡ ምንባቦች አላማቸው ተማሪዎቹ በቋንቋው የመግባባት ብቃታቸውን እንዲያዳበሩ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ዓላማ ለማሳካት በመማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ተቀንጭበው የሚቀርቡ ምንባቦች በአግባቡ ተፈትሸውና ተገምግመው መቅረብ አለባቸው፡፡ ይህም ሲባል ምንባቦቹ የተማሪዎቹን ዳራ፣ ባህል፣ ፍላጎትና ተነሳሽነት ወዘተ የመሳሰሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች መሰረት በማድረግ መመረጥ እንደሚገባቸው ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ይህንን ሀሳብ Sheldon (1988) የቋንቋ ክሂሎችንና የእውቀት ዘርፎችን ለማስተማር በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍት ውስጥ ምንባቦችን መርጦ ማካተት የመማር ማስተማር ሂደቱ የተሳካ እንዲሆን ከፍተኛ ሚና እንደሚጫዎት ይገልፃል፡፡

በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍት ውስጥ ተካተው የሚቀርቡ ምንባቦች ተማሪዎች የሚፈለገውን የቋንቋ ትምህርት ክህሎት እንዲጨብጡ ከፍተኛ እገዛ ሊያደርጉ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ እንደ Byrd (2001) ገለፃ የቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ተፈላጊ ውጤት ሊያገኝ የሚችለው ምንባቦቹ የተለያዩ መረጃዎችን የያዙ እንደሆኑ ያስረዳል፡፡ በተጨማሪም እንደ Ivannia (2007) ገለፃ ተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎችን እንዲያዳብሩ ማስቻል ከቋንቋ ትምህርት አላማዎች አንዱ ሲሆን፣ እነዚህን የቋንቋ ክሂሎች ለማስተማር የሚያስችሉ ተገቢነት ያላቸውን ምንባቦች መምረጥ ከባድ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ተግባር መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚሆኑ ምንባቦች በአጋጣሚ የሚመረጡ ሳይሆኑ በጥናት ላይ የተመሰረተ፣ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ተግባር መሆኑንና ምንባቦች በሚመረጡበት ወቅት ትኩረት ሊደረጉባቸው የሚገቡ መስፈርቶችን ዘርዝረዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ከተማሪዎች ጋር የተያያዙ የመምረጫ መስፈርቶች፤ የተማሪዎች ፍላጎት፣ ተነሳሽነት፣ የእውቀት ዳራና የክፍል ደረጃ ሲሆኑ ከሚመረጠውም ንባብ ጋር የተያያዙ መስፈርቶች ደግሞ እውናዊነት፣

ተነባቢነት፣ የቋንቋ ይዘትና የተለያዩ መልመጃዎችን ለማዘጋጀት ያላቸው አመችነት እንደሚጠቀሱ አስረድተዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ Dubin and Olshtain (1988) በቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች የመምረጥና የማደራጀት ጉዳይ ከባድ ጥረትን የሚጠይቅ መሆኑን ገልፀው፣ ምንባቦች በሚመረጡበት ጊዜ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ መስፈርቶችን ዘርዝረዋል፡፡ እነዚህም መስፈርቶች ወቅታዊነት፣ ግልፅነት፣ ተነባቢነትና የደረጃ መጣኝነት ወዘተ ሲሆኑ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥም መስፈርቶችን መሰረት ያደረጉ ምንባቦች ቢቀርቡ የተሻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

አንድ ምንባብ ተገቢነት አለው የሚባለዉ መስፈርቶችን አሟልቶ የቀረበና ተማሪዎች በቀላሉ አንብበው የሚረዱትና የማንበብ ክሂላቸዉን የሚያዳብር ሲሆን ነዉ::

የጥናቱ ዋና ትኩረትም Dubin and Olshtain (1988) በገለፁት ከላይ የቀረቡ ንድፈ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ በ2015 ዓ.ም በታተመውና በአሁኑ ጊዜ አገልግሎት በመስጠት ላይ ባለው በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦችን ተገቢነት መፈተሽ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ አዲስ መፅሃፍ ዉስጥ የተካተቱት ምንባቦች ያላቸውን ወሳኝ ሚና ከግምት ዉስጥ በማስገባት ክሂሎትን ለማዳበር የሚያስፈልጋቸዉን የተገቢነት መስፈርቶች የሚያማሉ መሆናቸዉን በስርአት መመርመር አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ነው::

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ተማሪዎች በቋንቋ ክሂሎች የመግባባት፣ በተሳለጠ መንገድ መረጃ የመለዋወጥ ችሎታቸውን ማዳበር ነው፡፡ ሊዳብሩና ትልቅ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገባቸውም ክሂሎች አንዱ የማንበብ ክሂል ነው፡፡ ከቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች መካከል የማንበብ ክሂልን ማዳበር አንዱ ቢሆንም እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የተካሄዱ ጥናቶች የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዳልዳበረ ነው፡፡ በሙሉ (2009) የቀረበ ጥናትም ተማሪዎች በምንባብ ውስጥ የቀረቡ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን የመለየት የሃሳብ ትስስሩን የመረዳት ችግር እንዳለበት የጥናቱ ውጤት ያረጋግጣል፡፡ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለመዳበር ደግሞ ለንባብ የሚሰናዱት ምንባቦች ተገቢነት የራሳቸው ድርሻ ሊኖር ስለሚችል መፅሃፉ ውስጥ የሚገኙትን ምንባቦች ተገቢነት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ለመፈተሽ መፈለግ ለአጥኚው አንደኛው አነሳሽ ምክንያት ሆኗል፡፡

ሌላው አነሳሽ ምክንያት ደግሞ መማሪያ መፅሃፉ አዲስ በመሆኑና በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በዚህ መፅሃፍ የተካሄደ ጥናት አለማጋጠሙ ነው፡፡ የዘርፉ ምሁራን እንደሚሉትም ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚዘጋጁ መማሪያ መፅሃፍት ከችግር የፀዱ

ሆነው ሊቀርቡ እንደማይችሉና ችግሮቹንም ለመፍታት በጥናት መዳሰስ እንዳለባቸው በ(Grant፣1988) የተገለፀውን ሃሳብ ዋቢ ማድረግ ለአጥኚው ሌላኛው አነሳሽ ምክንያት ሆኖታል፡፡ ምክንያቱም የአጥኚው ርዕስ ያተኮረበት መፅሃፍ የቅርብ ህትመት በመሆኑ መማሪያ መፅሃፉ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ለክፍል ደረጃው ተገቢነት ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን ለማወቅ መፈለግ ለጥናት አነሳሽ ምክንያት ሆኗል፡፡

ሌላው ደግሞ በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍት ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦችን መርጦ በመፅሃፉ ውስጥ ማካተት ከባድ ጥረትን የሚጠይቅ እንደሆነ፣ በሚመረጡበት ጊዜ ሊያሟቸው ከሚገቡ ጉዳዮች ተገቢነት አንዱ ተተኳሪ ጉዳይ እንደሆነ ከመስኩ ምሁራን Dubin & Olshtain (1988) ይገልፃሉ፡፡ ጉዳዩም የትኛውንም ምንባብ በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ በማካተት ማቅረቡ አግባብነት እንደሌለው ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም የጥናቱ ተተኳሪ መፃሕፉ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ተገቢነት ማረጋገጥ አግባብነት ያለው ጉዳይ በመሆኑ ርዕሰ ጉዳዩን ለማጥናት ሰበብ ሆኗል፡፡

ሌላው አነሳሽ ምክንያት ከአጥኚው ተሞክሮ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አጥኚው በተለያዩ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለ18 ዓመታት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህርነት አገልግሏል፡፡ በእነዚህ ዓመታትም የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ችግሮች እንዳሉበት አስተውሏል፡፡ የምንባብ ጥያቄዎችን በደንብ አለመመለስ፣ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን ከምንባብ ለማውጣት ያለመቻል ችግር፣ የምንባቡን ሃሳብ ያለመረዳት ችግሮችን አጥኚው ማስተዋል ችሏል፡፡ ለእነዚህ ችግሮች የምንባቦቹ የተገቢነት ችግር መንስኤ ሊሆን ይችላል በሚል ተገቢነታቸው ለማጥናት ሌላኛው ምክንያት ሆኖታል፡፡ የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1.በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ወቅታዊ ናቸውን ?

2.በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ግልጽነት ያላቸው ናቸውን ?

3. በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ተነባቢ ናቸው?

1.3.የጥናቱ ዓላማዎች

1.3.1 አጠቃላይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2015 ዓ.ም. በታተመው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ምንባቦች ተገቢነት መፈተሽ ነው። ከዚህ አጠቃላይ አላማ በመነሳት የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች እግብ ለማድረስ ጥረት ተደርገዋል::

1.3.2.ዝርዝር ዓላማዎች

1.በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ወቅታዊነት መፈተሽ

2.በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ግልጽነት መፈተሽ

3.በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ተነባቢነት መፈተሽ

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህጥናት ለተማሪዎች፣ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ለመፅሃፍ አዘጋጆችና ለአጥኝዎች ጠቃሚ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በመጀመሪያ የጥናቱ ዋና ተጠቃሚዎችተማሪዎች ናቸው፡፡ በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ምንባቦች የሚካተቱበት ዓላማ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበርና ገሃዱን አለም በተለያዩ ምንባቦች እንዲገነዙ ለማደረግ ነው፡፡ ይህን ለማሳካት የሚቻለው ደግሞ ለደረጃው ተገቢ ምንባቦች ሲቀርቡ ነው፡፡ ስለሆነም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚያስችሉ፣ በገሃዱ አለም ያሉ ጉዳዮችን በምንባቦች እንዲያገኙና እንዲገነዘቡ ለማድረግ፣ የአስተሳሰብ አድማሳቸውን እንዲያሰፉ የሚያስችሉ ተገቢ ምንባቦችን ለማቅረብ ይጠቅማል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ የመፅሃፍ አዘጋጆችና አጥኝዎችም ተጠቃሚዎች ናቸው በተዋረድ፡፡

- ✓ **ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን** በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉ ምንባቦች ለተመደቡበት የክፍል ደረጃ ተገቢ መሆናቸውን እንዲፈትሹ፣ የምንባቦቹን ጥንካሬና ድክመታቸውን እንዲያውቁ ይጠቅማል፡፡ ለተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ የሚስማሙ ተገቢነት ያላቸውን ምንባቦች እንዲያቀርቡ ያስችላል፡፡
- ➢ **ለመፅሃፍ አዘጋጆች**-በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የተካተቱ ምንባቦች ተገቢነታቸውን ጠብቀው እንደት መዘጋጀት እንዳለባቸው ጥቆማ ሊሰጥ ይችላል፡፡

- ✓ **ለአጥኚዎች.** በምንባብ ተገቢነት ዙሪያ ጥናት ለሚያካሂዱ ሰዎች እንደ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

1.5 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የተካሄደው በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ በቀረቡ ምንባቦች ላይ ነው። በመማሪያ መፅሃፉ ውስጥ በርካታ የእውቀትና የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶች ያሉ ቢሆንም ይህ ጥናት ግን በምንባቦች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ምንባቦች ሊፈተሹ ከሚችሉባቸው ጉዳዮችም ተገቢነት አንዱ ሲሆን ይህ ጥናትም በ2015 ዓ.ም በታተመው "የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦችን ተገቢነት በመፈተሽ" የተወሰነ ነው፡፡ የምንባቦቹን ተገቢነት ለመፈተሽም ጥቅም ላይ የዋሉ የመገምገምያ መስፈርቶች በGuba and Lincoln (1989)፣ በKramsch (1993)፣ በTaylor (2004)፣ በCummins (2017)፣ በArias (2007)፣ በWilliam (2004)፣ በStrunk and white (1959) እና በJoseph (1990) የተገለፁትን ነው:: በነዚህ መስፈርቶች ላይ የተወሰነበት ምክንያትም የጥናቱን ርእሰ ጉዳይ ለመፈተሽ የሚያስችሉና የጥናቱን ውጤት በግልፅ የሚያሳዩ እንደሆነ በማመን ነው:: የምንባቦቹ ወቅታዊነት፣ ተነባቢነትና ግልፅነትን በመመርመር ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡

ጥቅም ላይ የዋሉት መመዘኛ መስፈርቶችም የምንባቦቹን ይዘት ከአከባቢያቸው ሁነት ጋር እንዲያይዙ የሚጋብዙ ባህላዊ ክንዋኔዎችን የሚገልፁ፣ ተማሪዎች ከሚኖርበት ማህበረሰብ ጋር የተቀራረቡ ጉዳዮችን የሚያንፀባርቁ፣ ተማሪዎች ከሚኖርበት ማህበረሰብ ጋር የተቀራረቡ ጉዳዮችን የሚያንፀባርቁ፣ የምንባቦቹ ዓረፍተ ነገረቹ ነጠላ አረፍተ ነገሮችና ግልፅ ሆነው የቀረቡበት፣ ዉስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን በብዛት ያልተጠቀሙ፣ የቃላት አጠቃቀማቸዉ መደበኛ የሆኑ፣ በደምብ የተደራጁና ተያያዥነት ያላቸዉ፣ የኢመደበኛ የቃላት አጠቃቀም ያላቸዉና በክፍል ደረጃዉ በቀላሉ አንብበው ለመረዳት የሚከብዱ ወይም የማይከብዱ መሆናቸዉን በመፈተሽ ላይ የተወሰነ ነበር::

1.6 የጥናቱ ውስንነት

ጥናቱ የተለያዩ ውስንነቶች አሉበት፡፡ በጥናቱ ርዕስ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች አለመኖር፣ በቂ አጋዥ ሃሳብ ያላቸው መፅሃፍ አለማግኘት ችግሮች ነበሩበት፡፡ የኢንተርኔት አቅርቦት ችግርና የስራ ጫና ለውስንነቱ የራሱ ድርሻ ነበራቸው፡፡ ለቃለመጠይቅ የመምህራን ፍቃደኝነት ውስንነት ነበረበት፡፡ ከአማካሪ የሚሰጡ የግምገማ ሃሳቦች አስራሩን እና ድክመቱን ያሳዩ ስለነበር ለጥናቱ ስኬት ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡

ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት

2.1. የንድፈ ሀሳባዊ ፅሑፎች ክለሳ

2.1.1. የመማሪያ መጻሕፍት ምንነት

በፅሑፍ ከሚቀርቡ የትምህርት መሳሪያዎች መካከል ዋነኛ ተጠቃሽ የመማሪያ መፃሕፍት ናቸው፡፡ እነዚህ የመማሪያ መፅሃፍት የመማር ማስተማር ሂደት በተገቢ መንገድ የታሰበለት ግብ ይመታ ዘንድ ከሚያግዙ መሳሪያዎች ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። ተስፋዩ (1981፡78) "የመማሪያ መፅሃፍ አንድ የተወሰነ ክፍልን እንዲያገለግል መሰረት በማድረግ የመማር ማስተማር ሂደት ሊያግዝ በሚችል መልኩ የተዘጋጀና ለታሰበው የትምህርት ዓይነት አንደ ዋና ምንጭነት የሚያገለግል መሳሪያ ነው፡፡ "በማለት ሲገልፁ፤ Grant (1987፡5) ደግሞ የቋንቋ መማሪያ መፅሃፍት የተደራጁ የተመጠኑና የቋንቋ ትምህርት አላማዎችን ከግብ ለማድረስ የተዘጋጁ ሰነዶች እንደሆኑ ይገልፃል፡፡

ከምሁራኑ አገላለፅ እንደምንረዳው መማሪያ መፃሕፍት ማለት በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች መርሃ ትምህርቱን መሰረት በማድረግ፣ የተማሪዎቹን እውቀትና ክህሎት ለማዳበር በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ዙርያ የሚዘጋጁ አጋዥና ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን የያዙ መፃሕፍት ናቸው።

Kifle (2009:56-57) "የመማሪያ መፃሕፍት የሚባሉት የመምህር መማሪያ፣ አጋዥ መፃህፍት፣ የተማሪ መፅሓፍ፣ መዝገበ ቃላት ወዘተ የመሳሰሉ የማስተማሪያ ማሳርያዎችን የያዙ ናቸው" በማለት አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም መማሪያ መፅሃፍት ማለት ለመማር ማስተማሩ አጋዥ የሆኑና በልዩ ልዩ ርእሰ ጉዳዮች ዙርያ የተፃፉ የተለያዩ መፅሓፍት ናቸው ማለት ይቻላል። የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት አላማቸው ደግሞ የቋንቋ ትምህርት አላማን ለማሳካት ማለትም የቋንቋ ክሂሎችን፣ የሰዋስውና የስነ-ፅሑፍን እውቀት ለማጎልበት (ለማሳደግ) ነው። በተጨማሪም የቋንቋ መማሪያ መፅሃፍት ተማሪዎች ስርአት ባለው መንገድ በቋንቋ ተገልጋይ እንዲሆኑ ማስቻል፤ በመርሀ ትምህርት ውስጥ ተማሪው ይማረዋል ተብሎ የተቀመጠውን ይዘት በተለያዩ መንገዶች እንዲማሩ ማድረግ፤ እንዲሁም የመምህሩና የተማሪው መማር ማስተማር ሂደት መረጃ በመስጠት የሚመሩትና ተማሪዎች አዳዲስ እውቀቶች፣ ፅንስ ሓሳቦች እንዲያገኙ በማድረግ ችግር የመፍታት ዓቅም የሚያጎልቱ ናቸው፡፡

2.1.2 የምንባብ ተገቢነት

የምንባቦችን ተገቢነት Richards & Schimdt (2002:575) እንዳስቀመጡት ከሆነ ተገቢነት (Validity) ምንም እንኳን ሰፊ ትርጉም ቢኖረውም በመማር ማስተማር ሂደት አንድን የተመረጠ ርእስ ተማሪዎች እንዲለማመዱ የተፈለገው የንባብ ክሂል ለማለማመድ የሚኖረው ብቃት ነው፤ ከዚህ አንፃር አንድ የተመረጠ ምንባብ የተፈለገው ዓላማ ከግብ የሚያደርስ ሲሆን ነው፡: የምንባብ ተገቢነት የሚረጋገጠው መፅሃፉ ሲዘጋጅ እንደ ዓላማ አንግቧቸው የተነሳ ተማሪዎች እነዚህ የተሰጧቸው ምንባቦችን ተምረው የተፈለገውን ዓላማ ሲያሳኩ ነው።

ከላይ ምሁራኑ ካቀረቡት ሀሳብ መረዳት የሚቻለው የምንባቦች ተገቢነት ደራሲው በፅሁፍ አማካኝነት ሊያስተላልፈው የፈለገውን መልእክት አንባቢዎች በትክክል መረዳት ሲችልና የጋራ መግባባት ሲኖር ነው። እንዲሁም በመማሪያ መፅሃፍት ተመርጠው የሚገቡ ምንባቦች የቋንቋ ክሂሎች ወይም የእውቀት ዘርፎችን ማዳበር በሚያስችል መንገድ ሲዘጋጁ፣ የሚፈለገውን ዓላማ ከግብ ማድረስ ከቻሉ ምንባቦች ተገቢነት አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ማለት በመማሪያ መፅሃፍ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ምንባቦች የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል የሚያዳብሩ ሆነው ከተረመጡ ተገቢነት አላቸው ማለት ነው፡፡

2.1. 3 በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የምንባብ አመራረጥ መስፈርቶች

በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ የምንባቦች አመራረጥ በሚመለከት በሚገባ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ጉዳይ ሲሆን፤ ምንባቦቹም የተማሪዎችን እድሜ፣ ፍላጎት፣ ባህላዊ ዳራ፣ የቋንቋ ችሎታቸውን ወዘተ መሰረት በማድረግ ቢመረጡ ተገቢ መሆኑን የተለያዩ ድርሳናት ያስገነዝባሉ ተስፋየ (1981፣88)፡፡ ‘የምንባቦቹ ይዘት ከተማሪዎች ዕድሜ፣ ፍላጎት፣ ከአከባቢያቸው ጋር የተጣጣመ፣ የአቀራረብ ስልታቸው ግልፅ የሆነ፣ የያዟቸው አዳዲስ ቃላት ክብደትና መጠን ከተማሪዎች ደረጃ ጋር የተጣጣመ መሆን እንደሞኖርበት ይገልፃል፡፡

በተጨማሪም በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያሉ ምንባቦች ለሌሎች ክሂሎች ማለትም ለማዳመጥ፣ ለመናገር፣ ለመፃፍና ቃላትን እንዲሁም ሰዋስውና ስነ-ፅሁፍን ለማስተማር በሚያስችል ዘዴ የተዘጋጁ መሆን አለባቸው፡፡

ቋንቋ የልዩልዩ ይዘቶች መግለጫ በመሆኑ ከይዘቶቹ ጋር የሚጣጣሙ ወይም ይዘቶቹን ለመግለፅ የሚያስችሉ ቃላትና ሀረጋት ለማስተማር እንዲያመቹ በማስተማሪያው መፅሃፍ ውስጥ የተቀመጡ የተለያዩ ይዘቶች ያላቸውም ንባቦች ሊኖሩ ይገባል

(ተስፋየ፣ 1981)፡፡ የይዘት መለያየት የአገላለፅ ስልት መለያየትንም ስለሚያስችል ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡ አንዱ ይዘት በትረካ ስልት፣ ሌላው ደግሞ በብያኔ ስልት የሚገለፅ ይሆናል፡፡

Byrd (2001) በበኩላቸው የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር ምንባቦች በጥንቃቄ አስቦ መምረጥ ይበልጥ ጠቃሚ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ አክለውም ተገቢነት ያላቸውም ንባቦች የመምረጥ ተግባር በተቻለ መጠን ውጤታማና ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ደግሞ በሰፊው ተአማኒነት ያላቸው መገምገሚያ መስፈርቶችን መጠቀም አስፈላጊ ነው በማለት አስረድተዋል፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ ጋር በማያያዝ Nuttall (1982) ይህንኑ ሃሳብ ሲገልፁ በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍት ዝግጅት ውስጥ የሚመረጡት ምንባቦች የትምህርቱን ሂደት መሰረታዊ ዓላማ ለማሳካትና ዓላማውን ከግብ ለማድረስ እንዲችሉ ከተማሪዎች ፍላጎት፣ ልምድና ችሎታ አንፃር የተገናዘቡና ተግባር ላይ ሲውሉ ተማሪዎችን በማንኛውም መንገድ የማያስቸግሩ መሆን እንዳለባቸው አስረድተዋል። ስለዚህ በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍት ዝግጅት ውስጥ የሚቀርቡት እነዚህም ንባቦች የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያሟሉ፣ ለተጨባጭ የህይወት ገጠመኛቸውም የቀረቡ እና በእነሱ የእውቀት ደረጃ ላይ የተገነቡ ሲሆኑ በእለት ተግባቦት ውስጥ ሊተገብሯቸውና ሊጠቀሙባቸው እንደሚችሉ ይገልፃሉ።

በመሆኑም ለቋንቋ ትምህርት የሚሆኑ ምንባቦች በምንመርጥበት ጊዜ የሚከተሉትን መስፈርቶች መሰረት ያደረገ ቢሆን ተመራጭነት እንዳለው የመስኩ ምሁራን ይጠቅሳሉ። እነዚህም ምንባቦች ተማሪዎቹ በቀላሉ አንብበው ሊገነዘቧቸው የሚችሉ፣ ሰዋስዋዊ መዋቅራቸውና ቃላቱ ለተማሪዎች የሚስማሙ፣ የተማሪዎችን ባህላዊ እሴት የጠበቁ ቢሆኑ የተሻለ እንደሆነ (Bright and McGregor, 1970) ያስገነዝባሉ። አክለውም በመማሪያ መፅሃፍት ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች ተማሪዎችን በአግባቡ ለማስተማርና የቋንቋ ክህሎታቸውን በቀላሉ እንዲያሳድጉ ለማድረግ ዓይነተኛ አስተዋፅኦ ይኖራዋል።

በዚህም ምክንያት ምንባቦች ሲመረጡ ከተማሪው ፍላጎት፣ ዕድሜና ችሎታ የሚስማሙ፣ ተማሪዎች የሚያውቋቸውና እንዲሰለቹ የማያደርጓቸውን፣ በጊዜ የተመጠኑ፣ እንዲሁም የሚያነሷቸው ርእሰ ጉዳዮች ወቅታዊና የተለያዩ ነገሮች ሊያስጨብጡ የሚያስችሉ መሆን እንዳለባቸው ገልፀዋል።

አንድ ምንባብ መርጠን በመማርያ መፅሐፍ ውስጥ ከማስገባታችን በፊት ሊተኮርባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች አሉ። ይህን በማስመልከት Nuttall (1982) አንድ ምንባብ መርጠን በመማርያ መፅሐፍ ውስጥ ከማስገባታችን በፊት የምንመርጣቸውም ንባቦች ተማሪዎችን በራሳቸው ፍላጎት አነሳሽነት እንዲያነቡ ያደርጋቸው ይሆን? ተማሪዎች የሚያውቁት ፅንሰ ሓሳብ በጥልቀት ያሳውቃቸው ይሆን? እንዲሁም ምንም የማያውቁትን ደግሞ ያሳውቃቸው ይሆን? በተጨማሪም ሌሎች ሰዎች እንዴት እንደሚያስቡ፤ ወይም ምንእንደሚሰማቸው ለመረዳት ያግዛቸው ይሆን? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ መሆን እንዳለበት ይገልፃሉ።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ ጋር በማያያዝም በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚካተቱ ምንባቦች የመምረጫ መስፈርት በተመለከተ በርካታ አጥኝዎች የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦችን ዘርዝረዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ Dubin and Olshtain (1988) በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍት ውስጥ የሚካተቱ ምንባቦች ወቅታዊት፣ ግልፅነት፣ የደረጃ መጣኝነትና ተነባቢነት ወዘተ የመሳሰሉትን መስፈርቶች መሰረት አድርገው ቢመረጥ የተሻለ መሆኑን እንደሚከተለው በቅደም ተከተል በዝርዝር ገልፀዋል፡፡

2.1.3.1 ወቅታዊነት

በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍት ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች ወቅታዊ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ወቅታዊነት ያለው ምንባብ ፅሁፉ ተመርጦ የቀረበበትን ወቅት (ጊዜ) ግምት ውስጥ ያስገባ ወይም ግንኙነት ያለው እንደሆነ Tefarra and Alemayehu (2019) ይገልፃል፡፡ ከወቅታዊነት አንፃር ምንባቦች ሲፈተሹም ከጊዜው ጋር የተያያዙ ባህላዊ ክንዋኔዎችን ማለትም ከጥምቀት፣ ከመስቀል ወዘተ ክብረ በዓላት ጋር፣ ከአዝዕርት (ከግብርና) ስራ ጋር ግንኙነት ያላቸው ምንባቦች ወቅታዊነት እንዳላቸው አክሎ ይገልፃል፡፡ ወቅታዊ ምንባቦች፣ ተማሪዎች ቋንቋቸውን ከባህላዊ ተሞክሮ ጋር እንዲያገናኙ የሚያግዙ፣ ቀደምት ማንነታቸውን እንዲረዱ የሚያስችሉ፣ እንደሆኑ የVigotsky ማህበረ ባህላዊ ንድፈ ሃሳብ ከላይ የተጠቀሰውን ንድፈ ሃሳብ ያጠናክራል፡፡

ሌላው ደግሞ ተማሪዎች የምንባቦቹን ይዘት ከአካባቢያቸው ሁነት ጋር እንዲያይዙ የሚጋብዙ ምንባቦች ወቅታዊነት ያላቸው እንደሆኑ Guba and Lincoln (1989) ይገልፃሉ፡፡እንደድርቅናዝናባማ የሆኑ ተፈጥሯዊ ክስተቶች ወይም አካባቢያዊ ለውጦችን በመግለፅ ተማሪዎች አካባቢያቸውን እንዲረዱ የሚያስችሉ መሆናቸውን በመገምገም ወቅታዊነታቸውን ማጤን እንደሚቻል Guba and Lincoln (1989) አክሎ ይገልፃሉ፡፡

ምንባቦቹ ሲዘጋጁ ከወቅቱ የሀገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ጋር መጣጣሙን መፈተሽ ይገባል፡፡

የአንድ ምንባብ ይዘት ወቅታዊነቱን አሟልተዋል የሚባለው ከወቅቱ የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተገቢው መንገድ ሲገናዘብ ብቻ ነው፡፡ ተማሪዎች ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች የሚያንፀባርቁ ምንባቦች መርጦ በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ማካተት በርካታ አወንታዊ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ለምሳሌ፡- ስሜታቸውን እንዲያንፀባርቁ፣ አዲስ ሀሳብ ለማፍለቅ እንዲነሳሱ፣ ስለ ዓለምና ስለ ሰው ልጅ ያላቸውን የአመለካከት አድማስ እንዲያሰፉ ማድረግ ወዘተ የመሳሰሉት ጠቀሜታዎች እንደሚኖራቸው Kramsch (1993) ያስረዳል፡፡

በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች ሁልጊዜ ተማሪዎች በአከባቢያቸው በሚያውቋቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ የሚመለከቱ ሊሆኑ ይገባል ወደ ሚለው ድምዳሜ መጠጋት ተገቢ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ አመላካከት ያፈነገጡ፣ የተለየ ባህልና ልማድ የሚያንፀባርቁ ይዘቶች ያሏቸውም ንባቦች ለቋንቋ ማስተማርያነት የሚቀርብበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል በማለት Kramsch (1993) ያብራራሉ፡፡

2.1.3.2 ተነባቢነት

ተገቢ የሆኑ ምንባቦች ተነባቢነት ያላቸው ናቸው፡፡ አንድ ምንባብ ተነባቢ ነው ሲባል ደግሞ አንባቢዎች በቀላሉ የሚረዱትና ሃሳቡን ማብራራት የሚችሉት እንደሆነ Flesch (1946) ይገልፃል፡፡ የአንድን ምንባብ የተነባቢነት ደረጃ ለማወቅ ከምንባቡ ውስጥ መጠናዊና አይነታዊ ሆነው በሚወሰዱ መረጃዎች ማረጋገጥ እንደሚቻል የዘርፉ ምሁራን ይመክራሉ፡፡ እንደ Flesch (1946) ገለፃ በምንባብ የተነባቢነት ቀመር (Readability Formula) ከአንድ ምንባብ ውስጥ የቃላት ብዛትን፣ የቀለም ብዛትን፣ የአረፍተ ነገር ብዛትን፣ አማካይ የአረፍተ ነገርና የቀለም ብዛትን መረጃ በመሰብሰብ የተነባቢነት ደረጃን ማጤን እንደሚቻል ይገልፃል፡፡

ሌላው የምንባብን የተነባቢነት ደረጃ ለማወቅ ደግሞ ከምንባብ ውስጥ በአይነታዊ መረጃ በሚወሰዱ ሃሳቦች ነው፡፡ የአንድን ምንባብ የተነባቢነት ደረጃ የሚፈተሽበት አንዱ መንገድ የምንባቡን ግልፅነትና ቀላልነት (Clarity and Simplicity) በመገምገም ነው፡፡ ምንባቡ የቀረበበት ቋንቋ መደበኛ ቃላት ከሆኑ፣ ከኢ መደበኛ የቃላት አጠቃቀም የፀዳ ከሆነ ተነባቢነት ያለው ምንባብ ነው፡፡ እንዲሁም የምንባቦቹ አረፍተ ነገሮች የአመሰራተት ሂደትም ሌላው የተነባቢነት መፈተሻ ነው፡፡ ይህም ሲባል ምንባቡ የቀረበበት አረፍተ ነገሮች አጭር ወይም ግልፅ ከሆነ፣ ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን በብዛት ካልተጠቀመ ጥሩ የተነባቢነት ደረጃ ያለው ምንባብ ነው፡፡

ሌላው ደግሞ በምንባቡ ውስጥ የቀረቡት ሃሳቦች በደንብ የተደራጁ፣ የሃሳብ ተያያዥነት ያላቸው ምንባቦች ተነባቢ እንደሆኑ William (2004) Strunk and white (1959) እና Joseph (1990) ይገልፃሉ፡፡

አንድ ምንባብ የአንባቢን ስሜት መቆጣጠር እንዲችል ቋንቋው በሚፈልገው የአፃፃፍ ስርዓት፣ ቅርፅና ይዘት ጠበቆ መቅረብ ይገባል፡፡ እንደ አልፋ ዩኒቨርሲቲ (2009) አገላለፅ ከሆነ አንባቢውን የማስደሰት ሃይል ያለው፣አንብቦ ለመረዳት ቀላል የሆነ፣ ከአሻሚነት የፀዳ ምንባብ ተነባቢነት እንዳለው ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ እንዲሁም በግልፅነት የተጠቀሱ ነጥቦች ካሟላ ምንባቡ ተነባቢነት ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ ማለትም በግልፅነት ስር ካየናቸው ነጥቦች ጋር በማስተሳሰር ምንባብን ከተነባቢነት አኳያ ስንመለከት ከቃላት እስከ ቋንቋ አገባብ ስርዓት ድረስ የምንመረምርበት ነው። በመሆኑም በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚዘጋጁ ምንባቦች ጥሩ የሆነ የቃላት አጠቃቀም፣ ያልተዛባ የሰዋስዋዊ አገባብ፣ የምንባቦች የተመጠነ ርዝማኔ፣ በፅሁፍ ላይ የሚታይ ቅርጽ አለመዛባትና የተስተካከለ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ያለውም ንባብ ተነባቢነት ሰለሚያተርፍ ምንባቦች በጥንቃቄ መምረጥ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡

በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገቡ ምንባቦች የርዝማኔ መጠን ለመማር ለማስተማር ሂደት በመርሃ ትምህርቱ ከተመደበው የጊዜ ገደብና ከተማሪዎች የንባብ ልምድ ዳራዊ ሁኔታ ጋር የሚኖራቸው ዝምድና በጥልቀት መፈተሽ ይኖርበታል፡፡ እጅግ የረዘሙ፣ ውስብስብና አመራማሪ የሆኑ፣ እንዲሁም አላስፈላጊ ገለፃዎችና ምልልሶችን የያዙ ምንባቦች ተማሪዎችን በማሰላቸት በተመደበው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተገቢውን የቋንቋ ትምህርት ተግባር ላይ እንዳያውሉት እንቅፋት ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡

አንድ ምንባብ ሲመረጥ በመርሃ ትምህርቱ ከታቀደው የቋንቋ ትምህርት ዓለማና የተማሪዎች ዳራዊ የንባብ ልምድና እውቀት ያገናዘበ ሆኖ፤ ነገር ግን ርዝማኔው በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስቸግር ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነት ምንባብ በሚያጋጥምበት ጊዜ በምንባቡ ላይ ለቋንቋ ማስተማሪያነት በሚያመች መንገድ ተገቢ ማስተካከያዎች በማድረግ በቅንጫቢ መልክ ወስደን ልንገለገልበት እንችላለን፡፡

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ምንባቦች ተገቢነትን ማግኘት ይችሉ ዘንድ ከተማሪው ደረጃ ልምድና ችሎታ ጋር በተገናዘብ መንገድ በጥንቃቄ ሊመረጡ ይገባል። እንደመስኩ ምሁራን አገላለፅ በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍት ምንባቦች ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ ከባድ ቃላት፣ የተዛባ የሰዋስዋዊ አገባብ አጠቃቀም፣ ምንባቡ ከሚገባው በላይ መርዘም፣ ከፅሁፉ ላይ የሚታይ የቅርፅ መዛባት የተሳሳቱ የምልክቶችና የስርአተ ነጥቦች

አጠቃቀም የምንባቡን ተነባቢነት ስለሚጎዱ ምንባቡ ሲመረጥ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ ከላይ ከተጠቀሰው ሐሳብ እንደምንረዳውም ንባቦች ሲዘጋጁ ከፍ ብለው ከተጠቀሱት ነጥቦች በተጨማሪ ከይዘታቸውም አንፃር መፈተሽ ይኖርባቸዋል። በተለይ ይዘት ላይ የተመሰረቱ ምንባቦችን መምረጥ ተማሪዎችን ከተለያየ የአፃፃፍና የአገላለፅ ስልት ጋር ከማስተዋወቁም ሌላ ሊፈጠር የሚችለውን መሰላቸት በከፍተኛ ደረጃ የሚቀንስ መሆኑን ነው።

የምንባቦቹ የቋንቋ ይዘት ከቋንቋ ትምህርት ዓላማ ጋር ያለው ዝምድና በአግባቡ መጠናት ይኖርበታል፡፡ እንደ Khelmlani (2004) አገላለፅ የምንባቦቹ የቋንቋ አጠቃቀም ተማሪዎች እንዲማሩትና እንዲያዳብሩት ከተፈለገው የቋንቋ ክህሎች ጋር ይጣጣማል ወይስ ይቃረናል የሚለውን ጥያቄ አስቀድሞ መመለስ የሚያስፈልግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ አክለውም ለክፍሉ ደረጃ የሚቀርቡ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚውሉ ምንባቦች ተቀዳሚው ዓላማ ተማሪዎች የምንባቦቹን ይዘት ተረድተው በተግባር እንዲተረጉሙ ብቻ ሳይሆን በመርሃ ትምህርቱ የታቀዱትን አላማዎች ለማሳካት የሚያግዙ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ለምሳሌ ያህል በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የሰፈረው ዓላማ ተማሪዎች በቋንቋው ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ ወዘተ እንዲችሉ ከሆነ የሚፈለገው የምንባቦቹ ይዘትም ከዚህ ዓላማ ጋር የሚስማሙ መሆን አለባቸው በማለት አስረድተዋል፡፡

2.1.3.3 ግልፅነት

በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች ግልፅነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ግልፅነት ያላቸው ምንባቦች፣ ምክንያታዊ የሆነ የሃሳብ ተያያዥነት ያላቸው፣ የታለመለት የክፍል ደረጃ እና እድሜ በቀላሉ አንብበው የሚረዷቸው እንደሆኑ Taylor (2004) ይገልፃል፡፡ እንዲሁም የቃላት አጠቃቀማውም ሆነ የአረፍተ ነገር አመሰራረታቸው ተገቢነት ያላቸው፣ የሃሳብ ውስብስብነት የሌላቸው፣ ኢመደበኛ የቃላት ምርጫ ያላቸውና ተገቢ ያልሆኑ የአረፍተ ነገር አወቃቀርን (Sentence structure) የተጠቀሙ ምንባቦች እንደሆኑ Cummins (2017) ይገልፃል፡፡ በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች ግልፅነት እንዳላቸው ለማረጋገጥም ሊተላለፍ የተፈለገን ጉዳይ በደንብ የገለፁ፣ በምሳሌ የተደገፉ ገለፃዎችን(ማብራሪያዎችን) የያዙ መሆናቸውን ማጤን እንደሚገባ Mayer (2009) ያስረዳል፡፡

በቋንቋ መማሪያ መፅሓፍ የሚቀርቡ ምንባቦች ግልፅና ተማሪው በሚረዳው መንገድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። የምንባቦች ግልፅነት የሚገለፀው ከሰዋሰው ግድፈት የጠራ፣ ከቋንቋ አጠቃቀም፣ ከአገልግሎት ውጭ ከሆኑ ከባድ ቃላት፣ ከቃላት አጠቃቀም፣ ከማያስፈልጉ የተዉሶ ቃላትና ከሰለቹ አገላለፆች የራቁ፣ የዓረፍተ ነገሮችና የአንቀፆች አወቃቀር ስርአት ጠብቆ በመገኘት፣ ተጠየቃዊ የሆነ አካሄድን የሚከተል የቃላት ምርጫን፣ የሀሳብ አገላለፅን በአግባቡ የያዘ ምንባብ ሲሆን ነው ግልፅነት አለው የሚባለው፤ ሰለዚህ እነዚህ ሁሉ ለተማሪው ግልፅ ሆነው መቅረብ አለባቸው፡፡

Glodbery (2007) እንደ ገለፁት ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚያገለግልም ንባብ በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ከተለመደው አጠቃቀም ያፈነገጡ አገላለፆች ጋር ያላቸው የትውውቅ ደረጃ ምን ያህል ነው? በምንባቦች ውስጥ የሚገኙ አዳዲስና ያልተለመዱ አገላለፆች ተማሪዎች የትኞቹን ያህል በቀላሉ ሊገነዘቧቸው ይችላሉ? የትኞቹንስ ያህል በቀላሉ አይገነዘቧቸውም? የሚለውን ጥያቄ መመለስ አስፈላጊ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ምንባቦቹ የተዋቀሩበት የቃላት ምርጫና ሰዋስዋዊ መዋቅር ከተማሪዎች የቋንቋ ክህሎት ጋር መጣጣሙን በአግባቡ መጠናት እንዳለበት ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ምንባቦቹ ይህንን ጉዳይ ከግምት ውስጥ ሳያስገባ የሚመረጡ ከሆነ በውስጣቸው የሚያዛቸው ፍቺዎች ለማወቅ አስቸጋሪ በሚሆኑ ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች አወቃቀር የተነሳ ተማሪዎች አስፈላጊውን የቋንቋ ተግባር ለማከናወን ችግር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች ታሪኩን የማንበብና የመገንዘብ ፍላጎታቸውን ሊቀንስ ይችላል፡፡ Arias (2007) ፡

ከዚህ በመነሳት ለቋንቋ ማስተማሪያነት ታስበው የሚመረጡ ምንባቦች የቃላት ክብደትና የሰዋስዋዊ መዋቅር ሁኔታ በአግባቡ መመርመር ይኖርበታል፡፡ ይህም ማለት በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ቃላትና የዓረፍተ ነገር መዋቅሮች ከተማሪዎች ዳራዊ እውቀት ጋር ያላቸው ዝምድና ምን ይመስላል? በምንባቡ ውስጥ ፀሃፊው የተጠቀመባቸው ቃላትና አገላለፆች የውርስ ቃላት፣ የአራዳ ቃላት፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮች፣ ዘየዎች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች ወዘተ በብዛት ይገኛሉ ወይ? የሚሉትን ሆነ ሌሎቹን ጥያቄዎች መመለስ አስፈላጊ ነው፡፡ ለተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ያልተለመዱና ለየት ያሉ የዓረፍተ ነገር አወቃቀችና የቃላት አጠቃቀሞች በብዛት የሚገኙ ከሆነ መልእክቱን ፈጥኖ ለመረዳት ሊቸገሩ ይችላሉ፡፡ በመሆነም ለነዚህ ጉዳዮች በመጠኑም ቢሆን የመምህሩ እገዛ ሊያቃልልላቸው ይችላል፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ በተጨማሪም ግልፅነትን በተመለከተ ተስፋዬ (1981፣94) እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡

ግልፅነት ሲባል የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ የያዟቸው የትምህርት ጉዳዮች መምህር እንዲያስተምር ለማገዝ በግልፅ መስፈርት አለመስፈራቸው የሚመዘንበት ነው። ግንዛቤ እንዲያገኙላቸው የቀረቡ የቋንቋ የትምህርት ጉዳዮች ምንነታቸው በማያሻማ ስልት እንዲቀርቡ ያስፈልጋል። እንዲሁም በማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አማካይነት ለትምህርት የቀረበው ጉዳይ ምንነትና የትምህርቱም ዓላማ ጭምር ግልፅነት እንዲኖራቸው ይጠበቃል።

2.1.3. 4 የደረጃ መጣኝነት

የአንድ ምንባብ ደረጃ መጣኝነት የሚለካው የተማሪውን ችሎታ ደረጃ በማገናዘቡ ነው። በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የሚካተቱ ምንባቦች ለተመደበው የክፍል ደረጃ ተማሪዎች ችሎታና ብቃትን መሰረት ያደረጉ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ተማሪዎች ከአቅማቸው በላይ የሆነ ምንባብ ሲያጋጥማቸው የማንበብ ፍላጎታቸውን ከመቀነሱም በላይ ግራ ሊያገባቸውም ይችላል፡፡ Dubin and Olshtain (1988) እንደሚያሳስቡት አንድ ምንባብ ሲዘጋጅ ከምንባቡ ውስጥ የሚቀርቡት ነጥቦች ምን ያህል ተማሪዎች አንብበው የሚረዷቸው የቃላቱ አገባብ ናየዓረፍተ ነገሮቹ አሰካክ የተለመደ መሆን፣ የተማሪዎችን ኣቅም፣ ችሎታና ደረጃ ለማገናዘብ የሚረዳ መሆን እንዳለበት ይገልፃሉ።
ተስፋዬ (1981) ስለምንባብ መጣኝነት ሲገልፁ ተማሪው የቋንቋ ችሎታው እንዲዳብር የሚቀርቡለት አዳዲስ ቃላት የተመጣጠኑና የዓረፍተ ነገር ቅንብሮችም የተወሰኑ እንዲሆኑ ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የሚቀርቡ ምንባቦች የተማሪው አቅም፣ የዕውቀትና የችሎታ ደረጃን ግምት ውስጥ ማስገባት ይጠበቃል፡፡ ለዚህም ምንባቦች ሲመረጡ ኣዳዲስ ቃላትና ሀረጋት ለየት ያሉ ሰዋስዋዊ አገባቦች መጥነው የሚያቀርቡ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚቀርቡ ምንባቦች ከተማሪዎች ዕድሜና ፍላጎት ጋር የሚዛመዱ መሆን አለባቸው፡፡ Serafini (2001) በበኩላቸው ለህፃናት፣ ለወጣቶች፣ ለጎልማሶች እንዲሁም እንደ የክፍል ደረጃቸው ሁኔታ የሚመጥኑ ምንባቦችን በመለየት መምረጥ አስፈላጊ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የሚመረጠው ምንባብ የተማሪዎቹን ቀልብ መሳብና የመማረክ አቅሙ ከፍ ያለ፣ ራሳቸውን የሚመለከቱበት፣ ከልምዳቸው አንፃርና ለህይወታቸው ካለው ቅርበት የተነሳ እንዲያነቡትና እንዲወዱት የሚጋብዝ ሊሆን እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡

በቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገቡ ምንባቦች ዋና ዓላማ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ተግባቦታዊ እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው፡፡ ተማሪዎች ይህንን ብቃት ማሳደግ እንዲችሉ ደግሞ የሚቀርቡት ምንባቦች ለዚሁ የክፍል ደረጃ በሚዘጋጀው መፅሃፍ ውስጥ ምሆነ ለቀዳሚውና ለተከታዩ ክፍሎች በሚዘጋጀው መፅሃፍ እርስ በርስ ተያያዥነት እንዲኖራቸው ማድረግ ሲቻል ነው ሲሉ weaver (2002) ይገልፃሉ፡፡

ለአንድ ቋንቋ ማስተማሪያ የሚያገለግሉ ምንባቦች የተማሪዎቹን የቋንቋ ችሎታ ግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ እንደሆነ Routman (2000) ይገልፃሉ፡፡ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ታስበው የሚመረጡ ምንባቦች የቋንቋ ይዘት በተማሪዎች አቅምና ችሎታ ላይ የተመሰረቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ አዘጋጆች ምንባቦችን ሲመርጡ ከተማሪዎች ችሎታ በታች ወይም ከፍ ያለ እንዳይሆን ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በምንባቦቹ ውስጥ አዳዲስና እንግዳ ቃላት ቢኖሩም እንኳ ትርጉማቸውን ተማሪዎች አውድ ላይ ተመስርተው ሊደርሱባቸው የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የምንባቦቹ ቋንቋ በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ከተለመደው የቋንቋ አጠቃቀም ያፈነገጡና ቃላትና አገላለፆች በስፋት የያዙ መሆን የለባቸውም፡፡ የምንባቦቹ ቋንቋና የአገላለፅ ስልት በአብዛኛው በቋንቋው ከተለመደው ስርዓት በእጅጉ ያፈነገጡ ሆነው ሲገኙ ተማሪዎቹን በማሰላቸት ተገቢውን የቋንቋ ተግባራት እንዳያከናውኑ እንቅፋት ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡

2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ የጥናት ርዕስ ጋር ቀጥተኛም ባይሆን በተጓዳኝ ግንኙነት ያላቸውን ጥናቶችን በመቃኘት ከዚህ ጥናት ጋር ያለውን አንድነትና መሰረታዊ ልዩነቶች የሚያስረዱ ሃሳቦች ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

የመጀመሪያው ከዚህጥናትጋር መጠነኛ ግንኙነት ያለው ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያነት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመጋቢው ኃ/ማርያም (2009) በ2004 ዓም በተዘጋጀው የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ በመማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦች የተነባቢነት ደረጃ ለመፈተሽ የተሰራ ጥናት ይጠቀሳል፡፡ የጥናቱ የአጠናን ዘዴው ዓይነታዊና መጠናዊን (ቅይጥ) ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ መረጃዎቹን በሰነድ ፍተሻ፣ በከፊል ነጻ ቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት አማካኝነት በመሰብሰብ በቁጥርና በገላፃ ስልት ተንትኗል፡፡ በመጨረሻም የምንባቦቹ የተነባቢነት ደረጃቸው ዝቅተኛ መሆኑን በጥናቱ ውጤት ላይ ጠቁሟል፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ተመርጠው የሚገቡ ምንባቦች የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያሟሉ፣ ወቅታዊ መረጃዎችን ያካተቱና በወጣቶች ሕይወትና ልምድ ላይ ተመስርተው ቢዘጋጁና ቢቀርቡ፣ ምንባቦች ተነባቢነት እንደሚኖራቸው ተጠቁሟል፡፡ እንዲሁም በየጊዜው በሚዘጋጁ አዳዲስ የማስተማሪያ መፅሃፍት ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች በማስተማሪያነት ከመቅረባቸው በፊት በተነባቢት መለኪያ ቀመሮች መመዘን ቢችልና ቀመሮቹም ለአማርኛ ቋንቋ ምንባቦች ተነባቢነት ያላቸው ተገቢነት በጥናት ቢደገፍ የሚል የመፍትሄ ሀሳብ ጠቁሟል፡፡

የመጋቢው የጥናት ዓላማ በተተኳሪው መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦችን የተነባቢነት ደረጃ መመርመርና የምንባቦች የንባብ ክብደትና ቅለት ከከፍል ደረጃው ጋር ያለውን ግንኙነት ማየት ላይ ያተኮረነው፡፡ ስለሆነም የመጋቢው ጥናት ከአጥኚው ጥናት ጋር በሰነድ ፍተሻና በቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ይመሳሰላል፡፡ ነገር ግን መሳሪያዎቹ በሚያነሱት ዝርዝር መለኪያ ነጥቦች ይለያያል፡፡ እንዲሁም መጋቢው ከሰነድ ፍተሻና ከቃለመጠይቅ በተጨማሪነት ቡድንተኮርውይይትን መጠቀሙ ከአጥኚው ጥናት ይለያል፡፡ ዋናው የልዩነታቸው ምንጭ ደግሞ የንዑስ ዓላማ ትኩረታቸው ነው፡፡

የመጋቢው ጥናትም ሆነ የአጥኚው ጥናት የምንባቦችን ተነባቢነት ለመፈተሽ ማለማቸው ያመሳስላቸዋል፡፡ ነገር ግን ተነባቢነትን በፈተሹበት መንገድና መለኪያ ነጥቦች በእጅጉ ይለያያሉ፡፡ መጋቢው የምንባቦችን ተነባቢነት ለመፈተሽ መረጃን በአሃዝ ሰብስቦ (በመጠናዊ መረጃ) የገመገመ ነው፡፡ አጥኚው ደግሞ የምንባቦችን ተነባቢነት ለመፈተሽ መረጃን በቃላዊ መረጃ ሰብስቦ (በአይነታዊ መረጃ) የፈተሸ መሆኑ፣ መመዘኛ ነጥቦቹ የተለያዩ መሆናቸው፣ ጥናቱ ያተኮረበት የክፍል ደረጃና የመፅሃፉ ህትመት የተለያየ መሆኑ፣ የአጥኚው ጥናት፣ ከመጋቢው ጥናት ይለያል፡፡ እንዲሁም መጋቢው የምንባቦች የንባብ ክብደትና ቅለት ከከፍል ደረጃው ጋር ያለውን ግንኙነት ለማሳየት ጥናቱ የደረሰበትን ውጤት በአሃዝ የጠቆመ መሆኑ፣ የአጥኚው ጥናት ደግሞ የምንባቦችን ወቅታዊነትና ግልፅነት የፈተሸ መሆኑ በጥናቱ ዓላማ ይለያያሉ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ግምገማ የተደረገው ጥናት በየማነ ገብረፃዲቅ (2009) “በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦች የመቀበያ ክሂሎችን ለማስተማር ያላቸው ተገቢነት” በሚል ርእስ የተሰራን ጥናት ነበር፡፡

የጥናቱ ዓላማ በመምህር መምሪያውና በተማሪው መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የቀረቡ ምንባቦች የመቀበያ ክሂሎችን ለማስተማር ያላቸውን ተገቢነት መመርመር ነው። የአጠናን ዘዴው ዓይነታዊ ምርምር ሲሆን በሰነድ ፍተሻና በፅሁፍ መጠይቅ መረጃን በመሰብሰብ በገለፃ የመተንተኛ ስልት ተንትኗል፡፡

የጥናቱ ውጤትም የማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያ ምንባቦች አብዛኞቹ ተማሪዎች የሚነበበውን አዳምጠው እንዲገነዘቡ የሚያስችሉና ከራሳቸው ልምድና ገጠመኝ ጋር አዛምደው ምላሽ እንዲሰጡ የሚያደርጉ የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች በተጠናከረ ሁኔታ ያካተቱ ናቸው፡፡ የመፍትሄ ሀሳብ ብሎ ያቀረበውም የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች የተማሪዎችን ስሜት በሚቀሰቅስ መልኩ አድርገው መፃሕፍት አዘጋጆች ቢያዘጋጁ። መምህራን በምንባቦቹ ያሉትን አዳዲስ ቃላት፣ ሐረጋት፣ ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ ንግግሮች ምንባቦቹ ከመነበባቸው በፊት ተማሪዎችን በማሳተፍ አስቀድሞ ፍቻቸውን መጠቆም ቢቻል በማለት ገልጿል።

የየማነ ገብረፃዲቅ ጥናት ከአጥኚው ጥናት ጋር ተገቢነትን የፈተሸ መሆኑ ያመሳስለዋል፡፡ ነገር ግን የማነ ገብረፃዲቅ ተገቢነትን ከማዳመጥ ክሂል ምንባቦች አንፃር የፈተሸ መሆኑ፣ በመምህር መምሪያውና በተማሪው መማሪያ መፃሕፍት ላይ ያተኮረ መሆኑ፣ አጥኚው ደግሞ ለማንበብ ክሂል የቀረቡ ምንባቦች ላይ ማትኮሩ፣ በፈተሸዉ የምንባብ አይነት፣ የክፍል ደረጃ ይለያያሉ፡፡ እንዲሁም የየማነ ጥናት በሰነድ ፍተሻና በፅሁፍ መጠይቅ መረጃን የሰበሰበ ሲሆን በሰነዱ አይነትና በተጠቀመው የፅሁፍ መጠይቅ ከአጥኚው ጥናት ይለያል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የተገመገመው ጥናት ደግሞ በመአዛ አብርሃ (2009) "በ11ኛ ክፍል የትግርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦች የማንበብ ክሂልን ለማስተማር ያላቸውን ተገቢነት መፈተሽ" በሚል ርእስ የተሰራን ጥናት ከአጥኚው ጥናት ጋር ያለውን አንድነትና መሰረታዊ ልዩነት የፈተሸ ነበር፡፡ የጥናቱ ዓላማ በተተኳሪው መፅሃፍ ያሉ ምንባቦች የማንበብ ክሂልን ለማስተማር ያላቸውን ተገቢነት መፈተሽ ሲሆን፣ አይነታዊ የምርምር ዘዴ በመከተል በሰነድ ፍተሻና ለመምህራን በቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ አማካኝነት መረጃን በመሰብሰብ በገለፃ ስልት ተንትናለች፡፡ የተገኘውም ውጤት በተጠቀሰው መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦች ከተማሪዎች ዳራ፣ ከምንባቦቹ ሳቢነትና ከምንባብ ደረጃዎች አንፃር ሲፈተሹ ከ 90% በላይ የሚሆኑት ምንባቦች የምንባብ ክሂልን ለማስተማር ተገቢ መሆናቸውን ገልፃለች፡፡

በመፅሃፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ውስጥ የተወሰኑት ከቅርፅ አንፃር ስፋት ስላላቸው ይዘታቸው እንዳለሆኖ ቅርፃቸው (ስፋታቸው) ቢስተካከሉ፣ እነዚህም ንባቦች ተማሪዎች በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ ለማንበብ ስለሚቸገሩ ሰፋ ያለ ጊዜ ቢሰጣቸው፡፡ የሚል የመፍትሔ ሃሳብም አቅርባለች፡፡

የአጥኚውና የመአዛ ጥናት ተገቢነት ላይ ማተኮራቸው ያመሳስላቸዋል፡፡ ነገር ግን በዓላማቸው ይለያያሉ፡፡ መአዛ የምንባቦችን ተገቢነት ከተማሪዎችዳራና፣ ከምንባቦቹ ሳቢነት አንፃር የፈተሸች ሲሆን አጥኚው ደግሞ ምንባቦችን ከወቅታዊነት፣ ከተነባቢነትና ግልፅነት አንፃር መፈተሹ፣ ጥናቱ የቀረበበት የክፍል ደረጃ፣ ዘመንና በመረጃ መሰብሰበያ መሳሪያ በእጅጉ ይለያያል፡፡

ምዕራፍ ሶስት፤የአጠናን ዘዴ

3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሓፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦች ተገቢነት መፈተሽ ነው፡፡ ዋና ትኩረቱ በ2015 ዓ.ም በታተመው ላይ ነው:: የጥናቱ አቅጣጫ አይነታዊ ሲሆን የትንተና ስልቱም ገላጭ ገምጋሚ ነው፡፡ ምክንያቱም ገላጭ ጥናት እንደ ያለው (2009) ገለፃ አንድን ጉዳይ አንስቶ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በትረካ የሚቀርብበት፣ ችግሮቹ ምን እንደሆኑና መነሻቸው ምንድን ነው ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ ነው፡፡ ይህ ጥናትም ከላይ በተጠቀሰው መፅሃፍ ዉስጥ የተገቢነት ችግሮች እንዳሉበትና እንደሌሉበት የሚፈትሽ በመሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን የጥናት ስልት (ንድፍ) ተከትለዋል::

3.2 የናሙና አመራረጥ

3.2.1 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

በናሙናነት የተመረጠው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መጽሃፍ ነው:: ይህ የትምህርት ደረጃ የተመረጠበት ምክንያት መፅሃፉ በ2015 ዓ/ም የተዘጋጀ በመሆኑ አዲስ ስለሆነ ከዚህ ቀደም በመፅሃፉ ዙሪያ የተጠና ጥናት ስለሌለ ነው:: በ2015 ዓ.ም በአዲስ መልክ ከተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፎችም የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍቶች ብቻ ይገኙበታል:: ስለሆነም ከነዚህ መማሪያ መፃህፍት በታራ የእጣ ናሙና አመራረጥ የ9ኛ ክፍል መማሪያ መፅሃፍ ተመርጠዋል::

3.2.2 የትምህርት ቤት የናሙና አመራረጥ

ለሰነድ ፍተሻው የሚያግዙ መረጃዎች በቃለ መጠይቅ ከመምህራን ተሰብስቧል፡ እነዚህ መምህራን ደግሞ አጥኝው በሚያስተምርበት ትምህርት ቤት የሚገኙ ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቱም በስውሓ ስዕሊዕ ወረዳ በወልዋሎ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን በአመቺ ናሞና እንዲመረጥ ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም ደግሞ አጥኝው ከስራ ቦታ ርቆ ለመሄድ ካለበት ኢኮኖሚያዊና የስራ ጫና ከባድ መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ትምህርት ቤትም በማስተማር ላይ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስድስት ሲሆኑ ሁሉንም ጠቅላይ ናሙና አመራረጥ በቃለ መጠይቁ ምላሽ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳርያዎች

የጥናቱ ዋና ኣላማ ከግብ ለማድረስ ኣገልግሎት ላይ የሚውሉት የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች ወሳኝ ናቸው። ስለዚህ በኣጥኚው የተሰበሰቡ መረጃዎች ትክክለኛና ኣስተማማኝ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተጠቅሟል። እነሱም የሰነድ ፍተሻ እና የመምህራን ቃለ መጠይቅ ናቸው።

3.3.1 የሰነድ ፍተሻ

ኣጥኚው ጥናት ለማካሄድ ከመረጣቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ዋናኛው የሰነድ ፍተሻ ነው። በሰነድነት የተፈተሸውም በ2015 ዓም ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው የኣማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ናቸው፡፡ በሰነዱ ዉስጥ የቀረቡት ምንባቦች የተፈተሸቱም በGuba and Lincoln (1989)፣ በKramsch (1993)፣ በTaylor (2004)፣ በCummins (2017)፣ በArias (2007)፣ በWilliam (2004)፣ በStrunk and white (1959) እና በJoseph (1990) የተገለፁ መመዘኛ ቸክሊስትን በመጠቀም ነዉ:: የፍተሻው ኣላማም የምንባቦቹን ተገቢነት ማረጋገጥ ነው፡፡ የመመዘኛ ነጥቦቹን ተገቢነት ለመረጋገጥ ጥቅም ላይ የዋለዉ የተገቢነት ኣይነትም ውጫዊ ተገቢነት ነው:: ምክንያቱም ዉጫዊ ተገቢነት ቸክሊስቱ በውስጡ የያዛቸው ሃሳቦች የሚፈለገዉን መረጃ መሰብሰብ የሚያስችል መሆን ኣለመሆኑን ከሙያዊ እይታ ኣስተያየት የሚሰጥበት ስለሆነ ነው:: ግምገማውም በምርምር መስክ ባሉ ሰዎች፣ በስራ ባልደረዎች ኣጥኝዉ ባዘጋጀዉ መለኪያዎች ላይ ኣስተያየት የሚሰጥበት እንደሆነ ያለው (2009) ይገልፃል:: በመሆኑም የመመዘኛ ነጥቦቹም ከላይ በተጠቀሱት ሙሁራን ተዘጋጅተው በኣጥኝው ተግባር ላይ ከመዋላቸው በፊት ተገቢነታቸው በኣማካሪና በኣቻ መምህራን እንዲገመገሙ ተደርጓል:: ለዋናው ጥናት ጥቅም ላይ የዋሉ የምንባቦችን ተገቢነት የመገምገምያ መስፈርቶችም በሰንጠረዥ ኣንድ እንዲሰፍር ተደርገዋል፡፡ በተጨማሪም በመማርያ መፅሃፉ ዉስጥ የሚገኙ ምንባቦች መረጃም በኣባሪ “ሐ” ስር ሰፍሮ ይገኛል፡፡

3.3.2 ቃለ መጠይቅ

በኣጋዥነት የተመረጠው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የመምህራን ቃለ መጠይቅ ነው። ቃለ መጠይቅ በኣንድ ጉዳይ ጥልቅ የሆነ ስፋት ያለውና የተብራራ ምላሽ ለማገኘት የሚያስችልና ለሰነድ ፍተሻው ማጠናከሪያ የሚሆን ነው፡፡ በመሆኑም በሰነድ ፍተሻ ኣማካኝነት የተገኘውን መረጃ የበለጠ ለማዳበር እንዲያስችል ኣማርኛ ቋንቋን ለሚያስተምሩ ስድስት መምህራን ቀርቧል፡፡ ለቃለ መጠይቅ የተዘጋጁት የጥያቄዎች ብዛት ዘጠኝ ናቸው፡፡

ጥያቄዎቹ በዝርዝር ዓላማዎቹና በክለሳ ድርሳን ላይ የምንባብን ተገቢነት ለመፈተሽ በሚያስችሉ ነጥቦች ላይ እንዲያተኩሩ ተደርጓል፡፡ ጥያቄዎቹ ከፊል የተዋቀረ ቃለመጠይቅ (Semi structured interview) በሚባለው የመጠይቅ ስልት እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም ይህ ስልት ተመራማሪው ለጥናቱ የሚያግዝ መረጃ ለማጠናቀር የሚያስችሉ፣ በጠቃሚ ጉዳዮች ላይ አትኩሮ ተጠያቂዎቹ መረጃ እንዲሰጡ የሚያስችል ከመሆኑም በላይ ተጨማሪ አስተያየት ካላቸው እንዲገልፁ እድል የሚሰጥ የቃለመጠይቅ አይነት ነው፡፡ ጥያቄዎቹ በአጥኚው ከተዘጋጁ በኋላም ተገቢነታቸውን ለማረጋገጥ በአቻ መምህራን እንዲመገሙ ተደርጋዋል፡፡ አስፈላጊውን ማስተካኪያም ተደርጎበታል፡፡

በቃለ መጠየቅ ሃሳብ የሰጡ መምህራንን አጠቃላይዳራ በአባሪ "ለ" እንዲሰፍሩ ተደርጓል፡፡ በመማሪያ መፅሃፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ባላቸው ተገቢነት ዙሪያ የሰጧቸውን ሃሳቦች በቃለ መጠይቅ የመረጃ ትንተና ክፍልና በሰነድ ፍተሻው ትንተናና ማብራሪያው በማጠናከሪያነት ቀርበዋል፡፡ ቃለ ምልልሶቹም የተካሄዱበት ዕለት፣ የወሰዱት ስዓትና የሰጡት ሃሳብ በአባሪ ‹‹መ›› ስር ቀርቧል፡፡

3.4 የመረጃ አሰባሰብና አደረጃጀት

በዚህ ጥናት መረጃ የተሰበሰቡት ከሰነድ ፍተሻና ከቃለ መጠይቅ ነው። የሰነድ ፍተሻ የመረጃ አሰባሰብ አጥኚው በመፅሓፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦች በአፅንኦት በማንበብ ያሉ ችግሮች በመረዳትና ለይቶ በማውጣት መረጃዎች በመመዘኛ መስፈርቶች ተሰብስቧል፡፡ የተሰበሰበው መረጃም በዓላማዎቹ ቅደም ተከተልና ፈርጅ ተደራጅተው ገላጭ ተንታኝ ስልት እንደተነተኑ ተደርጓል፡፡ ሌላው የተሰበሰበው መረጃ ደግሞ ለመምህራን ከቀረበ ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ነበር፡፡ በቃለ መጠይቅ ጥያቄዎቹም ለዓላማዎቹ መልስ የሚሰጡ መረጃዎች ቃለ መጠይቅ ከተደረገባቸው መምህራን በቃላት አማካኝነት በአጥኚው በድምፀ መቅረፅ ተሰብስቧል፡፡ የቃለምልልስ ሃሳቦቹንም በማዳመጥ ሃሳቦቹ ተቀናጅተው በወረቀት እንዲፃፉ ተደርጓል፡፡ መረጃዎቹም ከሰነድ ፍተሻው ጋር እየተገናዙ ገላጭ ተንታኝ ስልት እንደተነተኑ ተደርጓል፡፡

3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሓፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦች ተገቢነት መፈተሽ ነው። ስለሆነም በምንባቡ ውስጥ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ በሰነድ ፍተሻ እና ከመምህራን በቃለ መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎች በቃላዊ ገለፃ ተተንትነው እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡ አጥኚው ከሰነድ ፍተሻና

ለመምህራን ከቀረበው ቃለ መጠይቅ ያገኘውን መረጃ በቃላት ገለፃ የሰጠበት፣ በመሆኑ ገላጭ ተንታኝ ስልት እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

ምዕራፍ አራት፡- የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

ይህ ጥናት ዋና ዓላማው በ2015 ዓ.ም በታተመው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ምንባቦች ተገቢነት መፈተሽ ነው። ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችም በሰነድ ፍተሻና በቃለመጠይቅ ተሰብስቧል፡፡ በእነዚህ መሳሪያዎች የተገኙ መረጃዎችም የክለሳ ድርሳናት ሃሳቦችን እንደ ማንፀሪያ በመጠቀም እንዲተነተኑ ተደርጓል፡፡ ትንተናው የቀረበውም በገላጭ ተንታኝ ስልት ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ስልት እንደ ያለው (2009) ገለፃ ከቁጥር ይልቅ በቃላት የሚሰበሰቡ መረጃዎች የሚተነተንበት ስልት ስለሆነ ነው፡፡ የአጥኚው መረጃም በቃላዊ ማብራሪያ የቀረበ በመሆኑ ገላጭ ተንታኝ ስልት ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

4.1 የተጠኚው ሰነድ አጭር ቅኝት

ተጠኚው ሰነድ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪ መማሪያ መፅሃፍ ነው፡፡የታተመው በ2015 ዓ.ም ነው፡፡ አሳታሚውም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተር ነው፡፡ መፅሃፉ በጥበቡ እሸቴ (ፒ.ኤች.ዲ) እና በማንያለው አባተ (ፒ.ኤች.ዲ) የተዘጋጀ እና በታደሰ ሲባሞ (ፒ.ኤች.ዲ) እና በጌታቸው አዱኛ (ፒ.ኤች.ዲ) የተገመገመ ነው፡፡ የመማሪያ መፅሃፍቱ ውጫዊ ሽፋን ልዩ መገለጫ አለው፡፡ ሽፋኑ የተዋበው በአረንጓደ ቀለም፣ ከሽፋኑ ላይ ያሉት ፅሁፎች ‹‹አማርኛ እንደፌደራል ቋንቋ›› የሚል የመፅሃፉ ርዕስ፣ የተማሪው መፅሃፍና ዘጠንኛ ክፍል የሚሉ መረጃዎች በተለያየ የፊደል መጠን ተፅፎበታል፡፡ መጨረሻም የተረትና ምሳሌ እንዲሁም የፈለጣዊ ቃላትን ፍች በአባሪነት አቅርቧል፡፡

4.2 የጥናቱ የመረጃ ትንተና

በጥናቱ ተተኳሪ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦችን ተገቢነት ለመገምገም ከሰነድ ፍተሻና ከቃለመጠይቅ መረጃዎች ተሰብስቧል፡፡ መረጃዎቹ በገላጭ ተንታኝ ስልት ተተንትነው በቅደም ተከተል እንደቀርቡ ተደርጓል፡፡ ከሰነድ ፍተሻና ከቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በገለፃ መልክ ቀርዋል፡፡ ለትንተናው የሚያግዙ ከሁሉም ምንባቦች የተገኙት መረጃዎች በሚከተለው ሰንጠረዦች ሰፍሯል፡፡ የመረጃ ትንተናው በዝርዝር ዓላማዎቹ ቅደም ተከተል እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ሰንጠረዥ 1 በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፉ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦችን ተገቢነት በመገምገም የተገኙ መረጃዎች

መስፈርቶች	ዝርዝር መስፈርቶች	ም1	ም2	ም3	ም4	ም5	ም6	ም7	ም8	ም9	ም10
ወቅታዊነት	1.ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ይዘት የያዙ ምንባቦች	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ
	2.የምንባቦቹን ይዘት ከአካባቢያቸው ሁነት ጋር እንዲያይዙ የሚጋብዙ	ሀ	ሀ		ሀ		ሀ		ሀ		
	3.ባህላዊ ክንዋኔዎችን የሚገልፁ ምንባቦች							ሀ			
	4.ተማሪዎች ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋር የተቀራረቡ ጉዳዮችን የሚያንፀባርቁ ምንባቦች					ሀ				ሀ	ሀ
ግልፅነት	5.አመደበኛ የቃላት ምርጫ ያልተጠቀሙ ምንባቦች	ለ	ለ	ለ	ለ	ለ	ሐ	ሀ	ሐ	ሀ	ሐ
	6.በክፍል ደረጃው በቀላሉ አንብበው የሚረዷቸው ምንባቦች	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሐ	ሀ	ሐ	ሀ
	7.የሃሳብ ውስብስብነት የሌላቸው	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሐ	ሀ	ሐ	ሀ
ተነባቢነት	8.ተገቢ መጠን ባላቸው ነጠላ አረፍተ ነገሮች የተገነቡ ምንባቦች	ለ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ለ	ሀ
	9.ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን በብዛት የተጠቀመ ምንባቦች	ሐ								ሐ	
	10.ሃሳባቸው. ግልፅና ቀላል የሆኑ ምንባቦች	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ
	11.በደንብ የተደራጁ፣ የሃሳብ ተያያዥነት ያላቸው ሃሳቦችን የያዙ ምንባቦች	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ	ሀ

መግለጫ

ሀ. የመስፈርቶቹን ሃሳቦች ሙሉ በሙሉ ያሟሉ ምንባቦች

ከወቅታዊነት አንፃር፣ አንድ ምንባብ ሙሉ በሙሉ ሊያሟላቸው የሚገቡ ሃሳቦች በ‹‹ሀ›› የተገለፁት ከላይ በሰንጠረዥ 1 ከተራ ቁጥር 1-4 የቀረቡትን ነጥቦች ነው፡፡

ከግልፅነት አንፃር፣ አንድ ምንባብ ሙሉ በሙሉ ሊያሟላቸው የሚገቡ ሃሳቦች በ‹‹ሀ›› የተገለፁት ከላይ በሰንጠረዥ 1 ከተራ ቁጥር 5-7 የቀረቡትን ነጥቦች ነው፡፡

ከተነባቢነት አንፃር፣ አንድ ምንባብ ሙሉ በሙሉ ሊያሟላቸው የሚገቡ ሃሳቦች በ‹‹ሀ›› የተገለፁት ከላይ በሰንጠረዥ 1 ከተራ ቁጥር 8-11 የቀረቡትን ነጥቦች ነው፡፡

ለ. የመስፈርቶቹን ሃሳቦች በከፊል ያሟሉ ምንባቦች

ከወቅታዊነት አንፃር፣ አንድ ምንባብ በከፊል ሊያሟላቸው የሚገቡ ሃሳቦች በ‹‹ለ›› የተገለፁት ከላይ በሰንጠረዥ 1 ከተራ ቁጥር 1-4 የቀረቡትን ነጥቦች ነው፡፡

ከግልፅነት አንፃር፣ አንድ ምንባብ በከፊል ሊያሟላቸው የሚገቡ ሃሳቦች በ‹‹ለ›› የተገለፁት ከላይ በሰንጠረዥ 1 ከተራ ቁጥር 5-7 የቀረቡትን ነጥቦች ነው፡፡

ከተነባቢነት አንፃር፣ አንድ ምንባብ በከፊል ሊያሟላቸው የሚገቡ ሃሳቦች በ‹‹ለ›› የተገለፁት ከላይ በሰንጠረዥ 1 ከተራ ቁጥር 8-11 የቀረቡትን ነጥቦች ነው፡፡

ሐ. የመስፈርቶቹን ሃሳቦች ምንም ያላሟሉ ምንባቦች

ከወቅታዊነት አንፃር፣ አንድ ምንባብ ምንም ሊያሟላቸው ያልቻሉ ሃሳቦች በ‹‹ሐ›› የተገለፁት ከላይ በሰንጠረዥ 1 ከተራ ቁጥር 1-4 የቀረቡትን ነጥቦች ነው፡፡

ከግልፅነት አንፃር፣ አንድ ምንባብ ምንም ሊያሟላቸው ያልቻሉ ሃሳቦች በ‹‹ሐ›› የተገለፁት ከላይ በሰንጠረዥ 1 ከተራ ቁጥር 5-7 የቀረቡትን ነጥቦች ነው፡፡

ከተነባቢነት አንፃር፣ አንድ ምንባብ ምንም ሊያሟላቸው ያልቻሉ ሃሳቦች በ‹‹ሐ›› የተገለፁት ከላይ በሰንጠረዥ 1 ከተራ ቁጥር 8-11 የቀረቡትን ነጥቦች ነው፡፡

4.2.1 ከሰንድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች

የሰነድ ፍተሻውን መሰረት በማድረግ በዝርዝር ዓላማዎቹ ቅደል ተከተል ቀጥሎ **የትንታኔ ሃሳብ ቀርቧል፡፡**

4.2.1.1 በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ወቅታዊ ከመሆን ካለመሆናቸው አንፃር

በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ወቅታዊነት ያላቸውን ሃሳቦች የያዙ ምንባቦች እንዳሉ ከሰነድ ፍተሻው በተገኙ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡ አንድ ምንባብ ወቅታዊ ነው ወይም አይደሉም ብሎ ለመፈረጅ በGuba and Lincoln (1989) እና በKramsch (1993) የተገለፁ መስፈርቶችን በመመዘኛነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ከወቅታዊነት አንፃር የመለኪያ ሃሳቦቹም የምንባቦቹ ይዘት ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘቡ ሲሆኑ፣ የምንባቦቹን ይዘት ከአካባቢያቸው ሁነት ጋር እንዲያይዙ የሚጋብዙ ሲሆኑ፣ ባህላዊ ክንዋኔዎችን የሚገልፁ ምንባቦችና ተማሪዎች ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋር የተቀራረቡ ጉዳዮችን የሚያንፀባርቁ ምንባቦች ወቅታዊነት እንዳላቸው የሚገልፁ ናቸው፡፡

ለአተናተን እንዲመችም በመጀመሪያ የሁሉንም ምንባቦች የያዙትን ጥቅል ሃሳብ በመፈተሽ ወቅታዊነት ባላቸው ምንባቦች ላይ በመስፈርቶቹ መሰረት በየምዕራፎቹ ቅደም ተከተል ግምገማ ተደርጓል፡፡ የሰነድ ፍተሻው እንደሚያሳየው በምዕራፍ 1 ‹‹ባህላዊ ሽምግልና›› የሚል ምንባብ ከገፅ 4-6 ቀርቧል፡፡ ምንባቡ የተፃፈው በ2012 ዓም ሲሆን የሚያነሳው ሃሳብም ባህላዊ የሽምግልና ስርዓትን ፋይዳ የሚያወሳ ነው፡፡

ሃሳቡ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ከሚያዩት የሽምግልና ስርዓት ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ ተማሪዎች ፅሁፉን ሲያነቡ ይዘቱን ከአካባቢያቸው ሁነት ጋር እንዲያይዙ የሚጋብዝ መሆኑ፣ ከህትመት አመት አንፃርም በቅርብ የታተመ መሆኑ ወቅታዊ ነው፡፡

‹‹የሽማግሌው ምርቃት›› የሚል ምንባብ ደግሞ በምዕራፍ 2 ስር ቀርቧል፡፡ ምንባቡ ከገፅ 16-19 የሰፈረ፣ በ2003 ዓ.ም የታተመ፣ ስለሽማግሌ ምርቃት ፋይዳ የሚያወሳ፣ የሽምግልናው መንስኤ ቤተሰባዊ ግጭትን መነሻ ያደረገ በመሆኑ ግጭት ለትዳር መጠንከር ፋይዳ እንዳለውም የሚያወሳ ምንባብ ነው፡፡ ይህ ሃሳብ ተማሪዎቹ ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ህይዎት ጋር ግንኙነት ያለው፣ ስለትዳር ህይዎት በአካባቢያቸው የሚያጤኑት ጉዳይ ጋር የተያያዘ፣ ሃሳብ ማቅረቡ ወቅታዊ የሆነ ምንባብ ነው ወደሚል ድምዳሜ አድርሷል፡፡

በምዕራፍ 3 ደግሞ ‹‹ሳይንስና ቴክኖሎጅ ለዘላቂ ልማት›› በሚል ርዕስ የቀረበ ምንባብ ይገኛል፡፡ የምንባቡ ምንጭ የአማራ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጅና ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ሲሆን በ2009 ዓ.ም የተፃፈ፣ በመማሪያ መፅሃፉ ከገፅ 30-32 የሚገኝ ነው፡፡ ምንባቡ ለሃገር እድገት የሳይንስና ቴክኖሎጂ አስፈላጊነት ምን ያህል እንደሆነ ያትታል፡፡ የምንባቡ ሃሳብ ሳይንስ ለቴክኖሎጅው ፈጠራ አስፈላጊ ስለመሆኑ የሚገልፅ ነው፡፡ ይህም ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በማውሳቱና ከወቅቱ የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በመገናዘቡ፣ ወቅታዊነት ያለው መልዕክት የያዘ ምንባብ ነው፡፡ ስለሆነም የክፍል ደረጃውን ግምት ውስጥ ያስገባ ተገቢነት ያለው ምንባብ ነው፡፡

በምዕራፍ 4 ‹‹ወረርሽኝና ስነልቦናዊ ምላሾች›› የሚል ምንባብ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ከገፅ 41-44 ይገኛል፡፡ ምንባቡ በ2012 ዓ.ም በፅሃፊ ኖጎ ውብሸት በሃገራችን ኢትዮጵያ ተከስቶ የነበረውን የኮቪድ 19 በሽታን መሰረት አድርጎ የተፃፈ ነው፡፡በምንባቡ ውስጥ የተገለፀው መልዕክት ወረርሽኝ አስከፊ፣ ስነልቦናዊ ተፅዕኖ ያለውና ለበርካታ ሰዎች ህልፈት እንደሚዳርግ ያስረዳል፡፡ ይህ ሃሳብ በብዙ መልኩ ወቅታዊነት ያለው በመሆኑ ለክፍል ደረጃው ተገቢ የሆነ ምንባብ ነው፡፡ ምክንያነቱም የምንባቡ ይዘት ተማሪዎች በአካባቢያቸው ተከስቶ ከነበረ ሁነት ጋር የሚያያዝ መሆኑ፣ የቅርብ ክስተት በመሆኑ ወቅታዊ ነው፡፡

ከገፅ 54-56 ‹‹ፀሀይና ተግዳሮቶቿ›› በሚል ርዕስ በፅሃፊ ሻሂዳ ሁሴን በ2009 ዓ.ም ቀርቦ የምናገኘው አስረጅ ድርሰት ደግሞ በምዕራፍ 5 ስር ነው፡፡ ምንባቡ የሚያነሳው ሃሳብ ማየት የተሳናቸው ተማሪዎች ስለሚያጋጥሟቸው ችግሮች የሚገልፅ በመሆኑ ተማሪዎች ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋር የተቀራረቡ ጉዳዮችን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የይዘት ትኩረቱም ወቅታዊነት እንዳለው ያመላክታል፡፡

ከገፅ 68-70 በምዕራፍ 6 ስር ‹‹የተራቆተን አካባቢ ማልማት›› የሚል ምንባብ ቀርቦ ይገኛል፡፡ የምንባቡ ሃሳብ፣ የበርሃማነትን መስፋፋት መግታት ይቻላል ይላል፡፡ ምንባቡ የበርሃማነትን መስፋፋት መግታት እንደሚቻል በማስረዳት፣ ስነልቦናዊ ግንባታና ኢኖሚያዊ ፋይዳም እንዳለው የሚያስረዳ መሆኑ ከወቅቱ የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘበና ተማሪዎች ይዘቱን ከአካባቢያቸው ሁነት ጋር እንዲያይዙ ጋባዥ በመሆኑ ወቅታዊ ነው ወደሚል ድምዳሜ አድርሷል፡፡

በምዕራፍ 7 ‹‹ተበቺሳ›› የሚል የአንድን አካባቢ ባህልን የሚያስተዋውቅ ምንባብ ከገፅ 80-84 ቀርቦ ይገኛል፡፡ የምንባቡ ሃሳብ በደቡብ ወሎ አካባቢ የከንፈር ወዳጆች መገናኛ አጋጣሚዎች ከሆኑት መካከል የተበቺሳ ባህልን ማስተዋወቅ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጭብጡ ባህላዊ ክንዋኔዎችን በመግለፅ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ወቅታዊ ነው፡፡

ከገፅ 94-95 ‹‹ግብር መክፈል›› የሚል ምንባብ ደግሞ በምዕራፍ 8 ስር ቀርቧል፡፡ ምንባቡ ለደረጃው ወቅታዊ ነው፡፡ ምክንያቱም በክለሳ ድርሳን ላይ የቀረቡ ሃሳቦችን ዋቢ በማደረግ አንድ ምንባብ ከአካባቢው ሁነት ጋር የተያያዘ ሆኖሲገኝ ወቅታዊነት ያለው እንደሆነ በተገለው መሰረት ስለግብር መክፈል ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚያጤኑት ጉዳይ፣ የግብርን ምንጭና ጥቅም በቅርበት የሚረዱት ጉዳይ መሆኑ ምንባቡ ተማሪዎች ከሚያውቁት ጉዳይ የራቀ እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ በተማሪዎች ግንዛቤ የቀረበ ምንባብ ደግሞ ወቅታዊነት ያለው በመሆኑ ለክፍል ደረጃው ተገቢ የሆነ ምንባብ እንደሆነ ማጤን ተችሏል፡፡

በምዕራፍ 9 ስር ከገፅ 104-109 ድረስ የቀረበው ምንባብ ደግሞ በደራሲ በእውቀቱ ስዩም በ1994 ዓ.ም የተፃፈ ነው፡፡ ምንባቡ ልቦለድ ሲሆን ወላጆች ለልጆቻቸው ገመና ሲሉ የሚከፍሉትን መስዕዋትነት ይገልፃል፡፡ ወላጆች፣ ልጆቻቸውን አሳድገው፣ አስተምረውና ለቁም ነገር ካበቋቸው በኋላ ልፋታቸው በልጆቻቸው የማይመለስላቸው እንዳሉ ይገልፃል፡፡

ይህን የልጆችን ውለታ ቢስነት ደግሞ ገመናው ሊሸፈን እንደሚገባ ገላጭ ሃሳብ የያዘ የልቦለድ ድርሰት ነው፡፡ የምንባቡ ሃሳብ በየትኛውም ማህበረሰብ በሚገኙ በሩህሩህ ወላጆች እና በውለታ ቢስ ልጆች ላይ የሚከሰት ጉዳይን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ ልቦለዱ ምንም እንኳን በ1994 ዓ.ም የተደረሰ ቢሆንም ጭብጡ ግን ባለፈው፣ በአሁኑና ወደፊት በሚመጣው ትውልድ ላይ የሚታይን ስብዕና ገላጭ በመሆኑ ወቅታዊ ሃሳብን የያዘ ምንባብ ነው፡፡ ለክፍል ደረጃውም ተገቢነት ያለው ነው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን ጉዳዮች (ማህበራዊ ወይም ባህላዊ

ጉዳዮች) የሚገልፁ ምንባቦች ወቅታዊነት እንዳላቸው Kramsch (1993 የገለፀውን ሃሳብ ዋቢ በማድረግ ምንባቡ ወቅታዊነት ያለው ነው ወደሚል ድምዳሜ አድርሷል፡፡

በመጨረሻም በምዕራፍ 10 ከገፅ 120-121 ድረስ ‹‹የልማት አርበኛው ጀኔራል›› በሚል ርዕስ የቀረበ ምንባብ ይገኛል፡፡ ምንባቡ ምን ሃሳብ ይዟል? ከሃሳቡስ በመነሳት ወቅታዊነት አለው? ወይስ የለውም? የሚለውን ማጤን ተገቢ ነው፡፡ ምንባቡ በ2004 ዓም በደራሲ ብርሃኑ አለሙ በሪፖርተር ጋዜጣ ላይ የተፃፈ ነው፡፡ የያዘው ሃሳብም ስለስራ፣ ስለልማት አርበኝነት፣ የሰራ አርበኛ ሰው ደግሞ ጠንካራ ሰራተኛ እንደሆነ ጠንክሮ መስራትም ስኬታማ እንደሚያደርግ ይገልፃል፡፡ ይህ ይዘት ደግሞ ተማሪዎች በአካባቢያቸው በየዕለቱ ጠንክሮ በመስራት ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ከሚታዘቡት ጉዳይ ጋር በማያያዝ ስለሚረዱት ለደረጃው መቅረቡ ተገቢነት ያለው፣ የሚያስተላልፈውም ሃሳብ በአንድ ጊዜ ተሰምቶ የሚረሳ ሳይሆን፣ ሁሌም በሰው ልጅ ህይዎት ያለን ጉዳይ በመዳሰሱ ወቅታዊነት እንዳለው ያሳያል፡፡

ከላይ ከምዕራፍ አንድ እስከ አስር ድረስ የቀረቡት ምንባቦች ሃሳብ ከወቅታዊነት አንፃር ሲፈተሽ ሁሉም ምንባቦች ተገቢነት ያላቸው፣ ወቅታዊ ምንባቦች ናቸው፡፡ ምክንያቱም የእነዚህ ምንባቦች ሃሳብ ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘቡ፣ ይዘታቸውን ከአካባቢያቸው ሁነት ጋር እንዲያይዙ የሚጋብዙ፣ ባህላዊ ክንዋኔዎችን የሚገልፁና ተማሪዎች ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋር የተቀራረቡ ጉዳዮችን የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ ይዘታቸው በዚህ መንገድ የተቃኙ ምንባቦች ደግሞ ለደረጃው ተገቢነት ያላቸውና ወቅታዊ እንደሆኑ በክለሳ ድርሳን ላይ በዋቢነት የቀረቡት Tefarra and Alemayehu (2019)፣ Guba and Lincoln (1989)፣ Kramsch (1993) እና ይገልፃሉ፡፡

በእነዚህ ከምዕራፍ አንድ እስከ አስር ድረሰ የቀረቡት ምንባቦች ሃሳብ ወቅታዊነት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ለመምህራን ከቀረቡ የቃለመጠይቅ መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የምንባቦቹን ወቅታዊነት ለመፈተሽ ከቀረቡት የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች መካከል ምንባቦቹ ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘቡ መሆናቸውን የሚጠይቅ ጥያቄ አንደኛው ነበር፡፡ አስሩም ምንባቦች ወቅታዊነት እንዳላቸው ከምላሻቸው ማጤን ተችሏል፡፡ ለአብነትም ባህላዊ ሽምግልና፣ የሽማግሌው ምርቃት፣ ሳይንስና ቴክኖሎጅ፣ የልማት አርበኛው ምንባቦች ወቅታዊነት እንዳላቸው ጠንከር ያለ አስተያየት ከተሰጠባቸው ይጠቀሳሉ፡፡ ወቅታዊ እንደሆኑ አስተያየት የተሰጠባቸው ምንባቦች የቅርብ ጊዜ ህትመት ከመሆናቸው፣ ከተፃፉበት ወቅት ጋር ያለውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳይን ማቅረባቸው እንደሆነ በምክንያትነት ጠቅሰዋል፡፡ እነዚህ የቃለመጠይቅ መረጃዎችም ከሰነድ ፍተሻው ጋር ተደጋጋፊ ሆነዋል፡፡ ሁለተኛው ጥያቄ

ደግሞ ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ሁነት ጋር እንዲያይዙ የሚያስችሉ መሆናቸውን የሚጠይቁ ነበር፡፡ ከመምህራኑ ምላሽ ማጤን የተቻለው የሁሉም ምንባቦች ሃሳብ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ከሚያጤኑት ጉዳይ ጋር ግንኙነት እንዳላቸው ነው፡፡ ለአብነትም ስለልማት አርበኛው፣ ስለሳይንስና ቴክኖሎጅ የሚያቀርቡት ምንባቦች ተማሪዎች ከሚያውቁት ሃሳብ ጋር ግንኙነት እንዳላቸው አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ አጥኝው በስነድ ፍተሻ ላገኘው ውጤትም ማጠናከሪያ ሆኗል፡፡

4.2.1.2 በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ግልጽነት ያላቸው ከመሆን ካለመሆናቸው አንፃር

በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ተገቢነታቸውን ከግልፅነት አንፃር ለመፈተሽ በTaylor (2004)፣ በCummins (2017) እና በArias (2007) የተገለፁ መመዘኛ መስፈርቶች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የመስፈርቶቹ ሃሳብም የኢመደበኛ የቃላት አጠቃቀም ያላቸው ምንባቦች ከሆኑ የዘየ ቃላት፣ የተውሶ ቃላት፣ የሙያ ቃላት፣ ፈሊጣዊ ቃላት፣ የአራዳ ቃላትና ከባድ ቃላት የተካተቱባቸው መሆኑን በመፈተሽ እንዲሁም በክፍል ደረጃው በቀላሉ አንብበው ለመረዳት የሚከብዱ ወይም የማይከብዱ መሆናቸውን በማጤን ቀጥሎ ተገምግመው ቀርበዋል፡፡

በምዕራፍ አንድ ስር ‹‹ባህላዊ ሽምግልና›› ከሚለው ምንባብ ከተካተቱ ቃላት ተቀናቃኝ፣ ህልውናና ሉዓላዊነት የሚሉ ከባድ ቃላት ተካተው ይገኛሉ፡፡

ምዕራፍ 2 የሽማሌው ምርቃት ከሚለው ምንባብ ቆየ፣ ሰገግ፣ በየፊናችሁ የሚሉ ዘየ ቃላት ከገፅ 16-19 ድረስ የሚገኙ ሲሆን በገፅ 16 ላይ ልትሚያ የሚል ከባድ ቃል ተካትተው ይገኛሉ፡፡

በምዕራፍ 3 ሳይንስና ቴክኖሎጂ ለዘላቂ ልማት ከሚለው ምንባብ ቁርኝት፣ አውታሮች፣ አብዮትና ልዕለ የሚሉ ከባድ ቃላት በገፅ 32 ላይ፣ ኤሌክትሪክ፣ አውሮፕላን፣ ስልክ፣ ቴሌቨዥንና ኮንፒዩተር የሚሉት የሙያ ቃላት ገፅ 32 ላይ ይገኛሉ፡፡ በምዕራፍ 4 ወረርሽኝና ስነልቦናዊ ምላሾች ከሚለው ምንባብ እየዳረገ የሚል ከባድ ቃል፣ ሲሮቶኒን፣ ኬሚካል የሚሉ የሙያ ቃላት ከገፅ 41-44 ይገኛሉ፡፡ በምዕራፍ 5 ፀሀይና ተግዳሮቶቿ በሚለው ምንባብ ብሬል፣ ኦቲዝም፣ ስታለስና ኬን የሚሉ የሙያ ቃላት በገፅ 55 ላይ፣ መለማመጥ የሚል ከባድ ቃል እና ሰነባብቷል የሚል ዘየ ቃል በገጽ 55 ላይ ተካተው ይገኛሉ፡፡ በምዕራፍ 6፣ በምዕራፍ 8 እና በምዕራፍ 10 በሚገኙ ምንባቦች ኢመደበኛ የቃላት አጠቃቀም አይታይባቸውም፡፡ በምዕራፍ 7 ተበቺሳ በሚለው ምንባብ ውስጥ ከገፅ 80-84 ድረስ በርካታ ዘየ ቃላት ተካተዋል፡፡ እነሱም ጋሜ፣ ሳዱላ፣ ድንብሎ፣ የተወቀረ፣ ይበረበራል፣ አታሞ እና ድብል የሚሉት ተካተው ይገኛሉ፡፡ በዚሁ

በተጠቀሰው ገፅ ደግሞ እርጥብ ልምጭ፣ አጥንት ሰረሰረ፣ እና አጥንት ዘለቀ የሚሉ ከባድና ዘየ ቃላት ተካተው ይገኛሉ፡፡ በምዕራፍ 9 እናቲቱ በሚለው ምንባብ ከገፅ 104-109 ዘየና ከባድ ቃላት ተካተው ይገኛሉ፡፡ ከተካተቱ ዘየ ቃላት አረበበ፣ በቋጨበት፣ ኮቴውን፣ ባውንድ የሚሉ ዘየ ቃላት፣ ቱጃር፣ ገረመሙት፣ ጉራማይሌ፣ ተበቺሳ የሚሉት ከባድ ቃላት ይገኙበታል፡፡

ከላይ በተገመገሙት ምንባቦች የተጠቀሱት ቃላት ኢመደበኛ የቃላት አጠቃቀም ያላቸው ምንባቦች እንዳሉ መረዳት ተችሏል፡፡ በCummins (2017)፣ በTaylor (2004) እና በGlodbery (2007) የተገለፁት መመዘኛ ነጥቦች ደግሞ በመማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች ከዘየ ቃላትና ከተውሶ ቃላት፣ የፀዱ መሆን እንዳለባቸው ይገልፃሉ፡፡ እነዚህ ምንባቦች ደግሞ የዘየ ቃላትና የተውሶ ቃላት የያዙ በመሆናቸው ግልፅነቱ ተጓድሏል የሚል ድምዳሜ ላይ አድርሷል፡፡ በCummins (2017)፣ በTaylor (2004) እና በGlodbery (2007) ገለፃ በመማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች ከባድ ቃላት ከያዙ ግልፅነቱን እንደሚያጓድሉ ይገልፃሉ፡፡ ዋናው ጉዳይ ግን ምን ያህል ከባድ ቃላት መሆን አለባቸው የሚለው ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም እንደ Day (1994) ገለፃ በአንድ ገፅ ከሁለት በላይ ከባድ ቃላት ከተካተቱ ምንባቡ ከባድ ቃላት እንደያዘ ያስረዳል፡፡ እነዚህ ምንባቦች ደግሞ የያዟቸው ከባድ ቃላት የበዙ ስላልሆነ ከከባድ ቃላት አጠቃቀም አንፃር ችግር አይታይባቸውም፣ ለሃሳቡ ግልፅ አለመሆን ምክንያት አይሆንም ወደሚል ድምዳሜ አድርሷል፡፡

በመጀመሪያ በየምዕራፎቹ የተገመገሙት ኢመደበኛ ቃላት የትኞቹን ምንባቦች ለግልፅነት እንዳጋለጡ በተናጠል ማየቱ ተገቢ ነው፡፡ በምዕራፍ 6፣ በምዕራፍ 8 እና በምዕራፍ 10 የቀረቡት ምንባቦች ምንም አይነት የኢመደበኛ የቃላት የአጠቃቀም ችግር ስለሌለባቸው ግልፅነት ያላቸው ተገቢ ምንባቦች ናቸው፡፡ በምዕራፍ 1፣ በምዕራፍ 2፣ በምዕራፍ 3 እና በምዕራፍ 4 የቀረቡት ምንባቦች ያካተቷቸው ከባድ ቃላት፣ ዘየ ቃላት፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮችና የሙያ ቃላት አነስተኛ ቁጥር ያላቸው በመሆኑ የኢመደበኛ ቃላት አጠቃቀሙ ለግልፅነት የጎላ ችግር የማያመጡ እንደሆኑ ከሰነድ ፍተሻው መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በምዕራፍ 5፣ በምዕራፍ 7 እና በምዕራፍ 9 የቀረቡት ምንባቦች ግን በርካታ ዘየና የሙያ ቃላትን የያዙ በመሆናቸው የምንባቡን ግልፅነት የሚያጓድሉ ኢመደበኛ ቃላትን እንደያዙ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ በአስሩም ምንባቦች የተፈተሸው ጉዳይ አንብበው ለመረዳት የሚከብዱ ምንባቦች መኖር አለመኖራቸውን ነው፡፡ የምንባቡ ሃሳብ ቀላል የሆኑ ምንባቦችና ተማሪዎቹ መረዳት የሚችሉት ሆኖ ሲገኝ ግልፅነት ያለው ምንባብ እንደሆነ በክለሳ ድርሳን ላይ በCummins (2017)፣ በTaylor (2004) እና በGlodbery (2007) የተገለፁ ሃሳቦች ዋቢ ናቸው፡፡ በመሆኑም ምንባቡ ቀላል ሃሳብ በመያዝ ግልፅነት አላቸው ወይም የላቸውም ለማለት በቅድሚያ እያንዳንዱ ምንባብ ምን ሃሳብ ይዟል የሚለውን መፈተሽ ይገባል፡፡ ከባድ ሃሳብ ከያዙት ምንባቦች በምዕራፍ7 እና በምዕራፍ9 ስር የቀረቡት ይገኙበታል፡፡ ምክንያቱም በምዕራፍ 7 የቀረበው ምንባብ ስለአድስ ባህል ትውውቅ የሚያትት በመሆኑ፣ በምዕራፍ 9 የቀረበው ምንባብ ሰፊ የልቦለው ትረካ ያለው፣ የገፀ ባህሪያቱን ሃሳብ ከገሃዱ አለም ጋር ማያያዝን የሚጠይቅ፣ በበርካታ ዘየና ከባድ ቃላት የታጨቀ፣ በድርሰት ዐ/ነገሮች የተፃፈ መሆኑ ሃሳቡን ለመረዳት ከባድ በመሆኑ ግልፅ አይደለም ብሎ ማጠቃለል ተችሏል፡፡

ከምንባብ 7 እና ከምንባብ 9 ውጭ ያሉት ምንባቦች ግን ሃሳባቸውን ለመረዳት አይከብዱም፡፡ ምክንያቱም ለምሳሌ በምዕራፍ አንድ የቀረበው ምንባብ ስለሽምግልና የሚያወሳ በመሆኑ ጉዳዩ ለተማሪዎቹ የከበደ አይደለም፤ የሽምግልና ስርዓትን በአካባቢያቸው የሚያውቁት ጉዳይ ነውና፡፡

በሌሎቹም ምንባቦች የቀረበው ሃሳብ ከዚህ ገለፃ የተለየ አይደለም፡፡ ሃሳባቸውንም ለመረዳት የሚከብዱ ባለመሆናቸው ተገቢነት ያላቸው ወቅታዊ ምንባቦች ናቸው ወደሚል ድምዳሜ አድርሰዋል፡፡

የምንባብን ግልፅነት ለመፈተሽ የሚተኮርበት ሌላው በሶስተኛ ደረጃ የሚነሳው ነጥብ ሊተላለፍ የተፈለገን ጉዳይ በደንብ የገለፁና ምክንያታዊ የሆነ የሃሳብ ተያያዥነት ያላቸው ምንባቦች ግልፅነት ያላቸው እንደሆኑ በክለሳ ድርሳን ላይ የተገለፁ ሃሳቦችን ዋቢ በማድረግ በሁሉም ምንባቦች የቀረቡት ሃሳቦች በደንብ የተብራሩ ናቸው፡፡ ሁሉም ምንባቦች ዝርዝር ሃሳቦቻቸው ከዋናው ሃሳብ ሳያፈነግጡ የሚያትቱ እንደሆኑ ከሰነድ ፍተሻው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከላይ ከሰነድ ፍተሻው የተገኙትን ሃሳቦች የበለጠ ለማረጋገጥ በቃለ መጠይቅ በተገኙ መረጃዎች እንዲጠናከሩ ተደርጓል፡፡ የምንባቦቹን ግልፅነት ለመፈተሽ ለመምህራን የቀረበው አንደኛው ጥያቄ የምንባቦቹን የኢመደበኛ ቃላት የአጠቃቀም ጉዳይ የተመለከተ ነበር፡፡ ከመጠይቁ መረጃ ማጤን የተቻለውም በምዕራፍ 6 እና በምዕራፍ 10 የቀረቡት ምንባቦች ከኢመደበኛ የቃላት አጠቃቀም የፅዱ እንደሆነ ነው፡፡ በምዕራፍ 7 እና በምዕራፍ 9 ስር የቀረቡት ምንባቦች ደግሞ በርካታ ከባድ ቃላት፣ ዘየ ቃላትና

ፈሊጦች እንደ ተካተቱባቸው አስተያየት ቀርቧል፡፡ የቃለ መጠይቁ ምላሽም ከሰነድ ፍተሻው ጋር የሚደጋገፍ ሆኗል፡፡ ሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ ምንባቦቹ የያዙት ሃሳብ በቀላሉ አንብበው መረዳት የሚችሉት መሆኑን የሚገመግም ነበር፡፡ ከቃለ መጠይቁ መረዳት እንደ ተቻለው ተበቺሳና እናቲቱ የሚሉት ሁለት ምንባቦች አንብበው ለመረዳት እንደ ሚከብዱ፣ ከእነዚህ ውጭ ያሉት ምንባቦች ደግሞ የክፍሉ ደረጃ ተማሪዎች የሚረዱት ሃሳቦችን እንደያዙ አስተያየት ቀርቧል፡፡ ከቃለ መጠይቁ የተገኙት ምላሾችም የሰነድ ፍተሻውን ግኝት የሚያጠናክሩ ሆነዋል፡፡

4.2.1.3 በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ተነባቢ ከመሆን ካለመሆናቸው አንፃር

በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ተገቢነታቸውን ለማረጋገጥ የተተኮረበት ሌላው ጉዳይ ተነባቢነታቸውን በመገምገም ነው፡፡ ተነባቢነት ያላቸው ምንባቦች አረፍተ ነገሮቹ ነጠላ አረፍተ ነገሮችና ግልፅ ሆነው የቀረቡበት፣ ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን በብዛት ያልተጠቀሙ፣ የቃላት አጠቃቀማቸው መደበኛ የሆኑ፣ ግልፅና ቀላል የሆኑ፣ በደንብ የተደራጁና ተያያዥነት ያላቸው ሃሳቦችን

የያዙ እንደሆኑ በWilliam (2004)፣ በStrunk and white (1959) እና በJoseph (1990) የተገለፁ ሃሳቦችን በመመዘኛነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

ለአተናተን እንዲመች በቅድሚያ ከአረፍተ ነገር ጋር በተያያዙ ነጥቦች ዝርዝር የግምገማ ቀጥሎ ሃሳብ ቀርቧል፡፡ የሰነድ ፍተሻው እንደሚያሳየው ሁሉም ምንባቦች አረፍተ ነገሮቹ፣ ነጠላ አረፍተ ነገሮችና ግልፅ ሆነው የቀረቡባቸው፣ ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን በብዛት ያልተጠቀሙ፣ ስለመሆን አለመሆናቸው በየምዕራፎቹ ቅደም ተከተል ተፈትሸዋል፡፡ ከሰነድ ፍተሻውና ከቃለ መጠይቁ ማጤን እንደተቻለው ምንባቦቹ የተገነቡባቸው አረፍተ ነገሮች ተገቢነት የሌላቸው ምንባቦች አሉ፡፡ በአንፃሩ ደግሞ የአረፍተ ነገሮቹ አመሰራረት ተገቢነት ያላቸው ምንባቦች እንዳሉ ማጤን ተችሏል፡፡ ለምሳሌ በምዕራፍ1 ስር የቀረበው ‹‹ባህላዊ ሽምግልና›› የሚለው ምንባብ 45 አረፍተ ነገሮችን ይዟል፡፡ ከእነዚህ አረፍተ ነገሮች መካከል ምን ያህሉ ነጠላ አረፍተ ነገሮች ናቸው ምን ያህሉስ ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ናቸው የሚለውን ማጤን ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ምንባቦች በተገነቡባቸው አረፍተ ነገሮች ተገቢነታቸውን መፈተሽ ስለሚያስችል ነው፡፡ ስለሆነም ከላይ በተጠቀሰው ምንባብ ውስጥ 17 አረፍተ ነገሮች (37.7%) ያህሉ ነጠላ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ 28 (62.3%) አረፍተ ነገሮች ደግሞ ውስብስብ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ እንዲሁም በምዕራፍ 9 ስር እናቲቱ የሚለው ምንባብ 144 አረፍተ ነገሮች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም 59 (40.9%) ነጠላ አረፍተ ነገሮች፣

85 (59.1%) ያህሉ ደግሞ ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ ይህም የሚያሳየው ባህላዊ ሽምግልናና እናቲቱ የሚሉት ምንባቦች ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን በከፍተኛ መጠን እንደተጠቀሙ ነው፡፡

ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን በብዛት የተጠቀሙ ምንባቦች ደግሞ የተነባቢነት ችግር የሚነሳባቸው እንደሆኑ William (2004) Strunk (1959) and Joseph (1990) የተጠቀሱ መስፈርቶችን ዋቢ በማድረግ ምንባቦቹ የተገቢነት ችግር አለባቸው ወደሚል ድምዳሜ አድርሰዋል፡፡በሌሎች ምንባቦች ላይ ያሉት አረፍተ ነገሮች ግን ለተነባቢነት ችግር መንስኤ እንዳልሆኑ ማጤን ተችሏል፡፡ ለአብነትም በምዕራፍ 2 ካሉት 103 አረፍተ ነገሮች መካከል 73 (70.9%) ነጠላ አረፍተ ነገሮች፣ 30 (29.1%) ያህሉ ውስብስብ አረፍተ ነገሮች በምዕራፍ 3 ካሉት 39 አረፍተ ነገሮች 22 (56.4%) ያህሉ ነጠላና 17 (43.6%) ያህሉ ደግሞ ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ በምዕራፍ 4 ስር የቀረበው ምንባብ በ52 አረፍተ ነገሮች የተገነባ ሲሆን ከእነዚህም 27 (51.9%) ያህሉ ነጠላ አረፍተ ነገሮች፣ 25 (48.9%) ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡

በምዕራፍ 5 ካሉት 49 አረፍተ ነገሮች መካከል 28 (62.2%) ነጠላ፣ 21 (42.9%) ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ በምዕራፍ 6 ካሉት 45 አረፍተ ነገሮች 28 (62.2%) ያህሉ ነጣላ አረፍተ ነገሮች፣ 17 (37.8%) ያህሉ ደግሞ ውስብስብ በምዕራፍ 8 ካሉት 34 አረፍተ ነገሮች 16 (47.1%) ነጠላ አረፍተ ነገሮች፣ 18 (52.9%) ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ በመጨረሻም በምዕራፍ 10 የቀረበው ምንባብ በ40 አረፍተ ነገሮች የተገነባ ሲሆን ከእነዚህም አረፍተ ነገሮች መካከል 25 (62.5%) አረፍተ ነገሮች ነጠላ ሲሆኑ፣ 15 (37.5%) አረፍተ ነገሮች ደግሞ ውስብስብ ሆነው እንደተመሰረቱ የጥናቱ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ (ለበለጠ መረጃ አባሪ “መ” ይመልከቱ፡፡)

ከላይ በአሃዝ የተገለፁት የአረፍተ ነገሮች ብዛት ያላቸው አንድምታም ምንባቦቹ በርካታ በሆኑ ውስብስብ አረፍተ ነገሮች እንዳልተደረሱ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ምንባቦቹ ተነባቢነት ያላቸው እንደሆኑ ጠቁሟል፡፡

የምንባቦቹ ተነባቢነት የሚፈተሽባቸው ሌሎች ነጥቦች የመደበኛ ቃላት አጠቃቀማቸው፣ የሃሳባቸው ግልፅነትና ቀላልነት እንዲሁም ተያያዥ ሃሳቦችን የማቅረብ ያለማቅረባቸው ጉዳይ ተተኳሪ ነጥቦች እንደሆነ ከላይ ተጠቁሟል፡፡ አስሩም ምንባቦች ከተጠቀሱት መመዘኛዎች አኳያ ሲታይ ተገቢነት አላቸው፡፡ ከላይ በዓላማ 2 የምንባቦቹ ግልፅነት ሲፈተሽ የቃላት አጠቃቀማቸው ጉዳይ ተገምግሟል፡፡ በምዕራፍ 7 እና በምዕራፍ 9 ስር የቀረቡት ምንባቦች የኢመደበኛ ቃላት ችግር በስፋት ይታይባቸዋል፡፡

የቃላት አጠቃቀማቸው ኢመደበኛ የሆኑ ምንባቦች ደግሞ የተገቢነት ችግር የሚነሳባቸው በመሆኑ በምዕራፍ 7 ተበቺሳ የሚለው ምንባብና በምዕራፍ 9 እናቲቱ የሚለው ምንባብ ተገቢነታቸው ላይ ክፍተት እንዳለ መረዳት ተችሏል፡፡

ከሃሳብ ግልፅነትና ቀላልነት አንፃር ደግሞ በምዕራፍ 7 እና በምዕራፍ 9 ስር የቀረቡት ምንባቦች በበርካታ ዘየና ከባድ ቃላት በመቅረባቸው፣ የአረፍተ ነገር አመሰራረታቸው ወደ ውስብስብ አረፍተ ነገሮች የሚያደሉ በመሆናቸው የግልፅነት ችግር ያለባቸው፣ ሃሳባቸውንም ለመረዳት የሚፈትኑ እንደሆኑ ከሰነድ ፍተሻውና ከቃለመጠይቁ ማጤን ተችሏል፡፡

ከምዕራፍ 7 እና ከምዕራፍ 9 ውጭ ያሉት ምንባቦች ደግሞ አንብበው ለመረዳት ቀላል ሃሳብ የያዙ፣ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ከሚያውቁት ጉዳይ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ተነባቢነት ያላቸው እንደሆኑ ከሰነድ ፍተሻው ማጤን ተችሏል፡፡

ከምዕራፍ አንድ እስከ አስር ድረስ ያሉት ምንባቦች ተገቢነት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ለማረጋገጥ ለሰነድ ፍተሻው ማጠናከሪያ በሚሆኑ ሃሳቦች ማረጋገጥ ተችላል፡፡ ለመምህራን ከቀረቡት የቃለ መጠይቅ ምላሾች መረዳት እንደ ተቻለው ሶስት ምንባቦች በርካታ ቁጥር ባላቸው ውስብስብ አረፍተ ነገሮች እንደ ተመሰረቱ፣ ይህም ተነባቢነቱን የሚያጓድሉ እንደሆነ አስተያየት ቀርቦ ነበር፡፡ አስሩም ምንባቦች ሃሳባቸው በደንብ ተደራጅቶ እንደቀረበ፣ ዋናና ንዑስ ሃሳቦቹ ተያያዥነት ባለው መንገድ መቅረብ እንደቻለ በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ አጥኝው በሰነድ ፍተሻው ካገኘው መረጃ ጋር የሚደጋገፍ ሆኗል፡፡

4.2.2 ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች

1.በ2015 ዓ.ም በተዘጋጀው የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ከወቅቱ ተጨባጭ ሁነት የተገናዘቡ ናቸው ብለው ያምናሉ? ምሳሌ ቢጠቅሱ?

መ1. በእኔ አስተያየት ምንባቦቹ ወቅታዊ እንዲሆኑ ጥረት የተደረገባቸው ናቸው፡፡ በቅርብ ህትመት ላይ የተመሰረቱ፣ በተፃፉበት ወቅት ያለውን ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ገፅታ ማቅረባቸው ወቅታዊ ናቸው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡ ለምሳሌ በምዕራፍ1 ባህላዊ ሽምግልና የሚለው ምንባብ ከሚዳሰው ሃሳብ ማህበራዊ ጉዳይ አንዱ በመሆኑ፣ ባለንበት የአካባቢ አውድ የቀረቡ መሆናቸው የወቅታዊነቱ መገለጫ ነው ባይ ነኝ፡፡

መ2. ምንባቦቹ ወቅታዊ ናቸው፤ የሚያነሱት ጭብጥ ለህይዎታችን ቅርብ፣ ለማህበራዊ ህይዎታችን ጋር የተቆራኙ፣ በቅርብ ዓመታት የታተሙ በመሆናቸው ወቅታዊ ናቸው የሚልሃሳብ አለኝ የሚል ሃሳብ የሰጠ በመሆኑ ከመምህር አንድ ሃሳብ የተቀራረበ አስተያየት ሰጥቷል፡፡

መ3. ተበቺሳ ከሚለው ባህል አስተዋዋቂ ምንባብና እናቲቱ ከሚለው የልቦለድ ምንባብ ውጭ ያሉት ተማሪዎቹ በቀላሉ የሚረዷቸው ናቸው፡፡ የሚያነሱት ሃሳብም የሃገራችንን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ነው፡፡ ከዚህም አንፃር ወቅታዊ ናቸው የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡

መ4. ምንባቦቹ የቅረብ ክስተቶችን የሚያቀርቡ መሆናቸው የወቅታዊነታቸው ማሳያ ግምንባቦች የቅርብ ጉዳይ፣ በተጨባጭ ገሃዱ አለም ላይ ያሉ ጉዳዩችን ማቅረባቸው ወቅታዊ ናቸው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡ በምንባቦቹ በኢትዮጵያዊን ደራሲዎች በቅርብ ዓመታት መታተማቸው እንዲሁ የወቅታዊነት ማሳያቸው ነው፡፡

መ5.በእኔ አስተያየት ምንባቦቹ ወቅታዊ እንዲሆኑ ጥረት የተደረገባቸው ናቸው፡፡ በቅርብ ህትመት ላይ የተመሰረቱ፣ በተፃፉበት ወቅት ያለውን ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ገፅታ ማቅረባቸው ወቅታዊ ናቸው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡ ለምሳሌ በምዕራፍ1 ባህላዊ ሽምግልና የሚለው ምንባብ ከሚዳሰው ሃሳብ ማህበራዊ ጉዳይ አንዱ በመሆኑ፣ ባለንበት የአካባቢ አውድ የቀረቡ መሆናቸው የወቅታዊነቱ መገለጫ ነው ባይ ነኝ፡፡

መ6. ተበቺሳ ከሚለው ባህል አስተዋዋቂ ምንባብ ውጭ ያሉት ምንባቦች ተማሪዎቹ በቀላሉ የሚረዷቸው፣ የሃገራችንን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ማቅረባቸው ወቅታዊ እንደሆኑ ያሳያል የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡

2.በ2015 ዓ.ም በተዘጋጀው የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች፣ ይዘት ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ሁነት ጋር እንዲተዋወቁ የሚያደርጉ ናቸው? ምሳሌ ቢጠቅሱ?

መ1. እና መ3. ምንባቦቹ በአካባቢ ካሉ ክስተቶች፣ ጉዳዮች ጋር ቁርኝት አላቸው፡፡ የሽምግልና ስርዓትን የሚያወሳው ምንባብ በአካባቢ ካሉ የሽምግልና ስርዓት ጋር ግንኙነት አለው፡፡ የሽማግሌው ምርቃት የሚለው ምንባብ ምርቃት የሚያደርሱ አዛውንቶች(ሰዎች) በተለያየ አጋጣሚ ሰዎችን ሲመርቁ ከሚያዩት ድርጊት ጋር ግንኙነት አለው፡፡ የሁሉም ምንባቦች ሃሳብ ሲፈተሽ ተማሪዎቹ ከሚኖሩበት የአካባቢ ባህል፣ ድርጊት ወዘተ ጋር ቁርኝት እንዳላቸው ይገልፃሉ የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

መ2. የምንባቦቹን ሃሳብ ለመረዳት ከገሃዱ ዓለም ወይን ከአካባቢያቸው ሁነት ጋር ማያያዝ ተገቢነት አለው፡፡ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ደግሞ ከገሃዱ አለምና ከአካባቢው ሁነት ጋር አያይዘው እንዲረዷቸው ይጋብዛሉ፡፡ ስለልማት አርበኛው የሚገልፀው ምንባብ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ጠንካራ ሰራተኛ ከሆኑ ሰዎች ህይዎት ጋር እንዲያይይዙ ይጋብዛል፡፡

መ3. ምንባቦቹ ከአካባቢያዊ ሁነቶች ጋር ሃሳባቸውን አያይዘው እንዲረዷቸው ይጋብዛሉ፡፡ ለምሳሌ የልማት አርበኛ የሚለው ምንባብ በአካባቢ ካሉ ንቁ የልማት ሰራተኞች ጋር አያይዘው እንዲረዱት ይጋብዛል፡፡

መ5. ምንባቦቹ የሚያነሷቸው ሃሳቦች ከአካባቢያቸው አውድ ጋር ግንኙነት ያላቸው በመሆናቸው ሃሳባቸውን ለመረዳት አጋዥ ዳራ እንዳላቸው አስተያየት ሃሳብ ሰጥቷል፡፡

መ6. ምንባቦቹ የሚያነሷቸው ሃሳቦች ከአካባቢያቸው አውድ ጋር ግንኙነት እንዳላቸው፣ ሃሳባቸውንም ለመረዳት የሚረዳ የመነሻ ዳራ እንዳላቸው ተቀራራቢ ሃሳብ ሆኗል፡፡

3. በተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ባህላዊ ክንዋኔዎችን የሚገልፁ፣ ተማሪዎች ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋር የተቀራረቡ ጉዳዮችን የሚያንፀባርቁ ምንባቦች ቀርበዋል ብለው ያስባሉ ለምሳሌ

የዚህ ጥያቄ ምላሽ ከጥያቄ2 ጋር ተመሳሳይ ሃሳብ ያለው በመሆኑ ደጋግሞ መጻፍ አላስፈለገም፡፡

4. በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች የቃላት አጠቃቀማቸው አ. መደበኛ ናቸውን?

መ1. መ2. በመፅሃፉ ውስጥ የሚገኙት ምንባቦች የቃላት አጠቃቀማቸው መደበኛ ቃላትን ተጠቅመዋል፡፡ ጥቂት ምንባቦች ላይ ግን፣ ሃሳባቸውን ለመረዳት በጣም አዳጋች ባይሆንም አ.መደበኛ ቃላትን የያዙ ምንባቦች አሉ፡፡

መ3. በምዕራፍ 6 እና በምዕራፍ 10 የቀረቡት ምንባቦች ከዘየ፣ ከሙያ እና ከአራዳ ቃላት የፅዱ ናቸው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ተበቺሳ የሚለው ምንባብ በርካታ አ.መደበኛ ቃላት አሉት የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

መ4. ምንባቦቹ በአብዛሃኛው አስረጅ ድርሰቶች ናቸው፡፡ሲፃፉም የቃላት አጠቃቀማቸው መደበኛ ለማድረግ ጥረት እንደ ተደረገ ምሳሌ የሚሆኑ ምንባቦች አሉ፡፡

ለምሳሌ የልማት አርበኛው፣ የሽማግሌው ምርቃት የሚሉት ምባቦች ከኢመደበኛ ቃላት የፀዱ ናቸው፡፡ ተበቺሳና እናቲቱ የሚሉት ምንባቦች በርካታ ዘየ፣ ፈሊጣዊና ከባድ ቃላትን ይዘዋል፡፡

መ5. እና መ6. ብዙዎቹ ምንባቦች የሃሳብ ግርታን በማይፈጥሩ፣ የተግባቦት ክፍተት በማያመጡ መደበኛ ቃላት የቀረቡ ናቸው፡፡ አንዳንድ ምንባቦች ደግሞ የሙያ ቃላትን ከተጠቀሙ ሳይንስና ቴክኖሎጅ የሚለው ምንባብ፣ ዘየቃላት ከተጠቀሙ እናቲቱ የሚሉት ምንባቦች ይጠቀሳሉ፡፡

5. በዘጠንኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች የሃሳብ ውስብስብነት የሌላቸውና በቀላሉ አንብበው መረዳት የሚችሏቸው ምንባቦች ተመርጠዋል? ምሳሌ ቢጠቅሱ?

መ.1 በእኔ አስተያየት የብዙዎቹ ምንባቦች በቀላሉ አንብበው መረዳት የሚችሏቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ የምዕራፍ አንድ ምንባብ ስለሽምግልና ፋይዳ የሚያወሳ ነው፡፡ ይህ ተማሪዎች ባሉበት አካባቢ ሽማግሌዎች ሰዎችን ሲያስታርቁ የሚያዩት ቅርብ ጉዳያቸው ስለሆነ ለመረዳት ቀላል ነው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

መ.2 ዝርዝር ሃሳብ ለመስጠት ግን ሁሉንም ረጋ ብሎ ማንበብን የሚጠይቅ ቢሆንም ለአብነት ስለወረርሽኝ የቀረበው ምንባብ አንብበው መረዳት አይከብድም፡፡ ስለተበቺሳ የሚገልፅው ምንባብ ተማሪዎች ከሚያውቁት ባህል ጋር ግንኙነት አለው የሚያስብል አይመስለኝም፡፡ አንብበው መረዳት ከባድ ነው፡፡

መ.3 ስለሳይንስና ቴክኖሎጅ፣ ፅሃይና ተግዳሮቷ የሚገልፁት ምንባች አንብበው መረዳት ቀላል ናቸው፡፡ ምክንያቱም ለምሳሌ የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ተማሪዎች በትምህርታቸው የሚገጥማቸውን ችግር በአካባቢያቸው የሚታዘቡት ጉዳይ መሆኑ በቀላሉ አንብበው መረዳት ያግዛቸዋል የሚል ሃሳብ ሰጥቷል፡፡

6. በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች አረፍተ ነገር አመሰራረታቸው ምን ይመስላል? በነጠላ ወይስ በውስብስብ አረፍተ ነገሮቹ የተመሰረቱ ናቸው ? ምሳሌ ቢጠቅሱ

መ1. እና መ2. ሁሉም ምንባቦች ነጠላና ውስብስብ አረፍተ ነገሮች አሏቸው፡፡ የትኛው እንደሚበዛ ግን ምንባቦች በእርጋታ ማንበብን ይጠይቃል፡፡ በምዕራፍ 9 እናቲቱ የሚለው ምንባብ ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ይበዛበታል የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

መ3. እና መ6. አብዛኛዎቹ ምንባቦች ላይ ነጠላ አረፍተ ነገሮች በዝተው ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ ሳይንስና ቴክኖሎጅ የሚለው ምንባብ ብዙ ነጠላ አረፍተ ነገሮች አሉት፡፡

መ4. ይህ ጉዳይ በደንብ ጊዜ ወስዶ መፈተሽ ያለበት ይመስለኛል፡፡በቅድሚያ አንድን ምንባብ ብቻ ወስደን ብናይ በጥቅሉ ስንት አረፍተ ነገሮች እንዳሉት ከታወቀ በኋላ ስንቶቹ ነጠላና ውስብስብ እንደሆኑ ማጤን ይቻላል የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

መ5. ይህ በጥልቀት ተቆጥሮ ቢታይ ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ በምዕራፍ1 ያለው ምንባብ የነጠላ አረፍተ ነገሮቹ ቁጥር ከውስብስብ አረፍተ ነገሮቹ ይበልጣል የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

7.በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉ ምንባቦች በደንብ የተደራጁ፣ የሃሳብ ተያያዥነትና ግልፅነት ያላቸው ሃሳቦችን የያዙ ናቸው ምሳሌ ቢጠቅሱ

መ1. በእኔ እተያየት ሁሉም ምንባቦች የሃሳብ ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች አቅርበዋል፡፡ ለምሳሌ ባህላዊ ሽምግልና የሚለው ምንባብ ስለባህላዊ ሽምግልና ምንነት፣ ፋይዳ፣ የሚፈታቸው ጉዳዮችና የሽምግልና ሂደቶችን ሃሳባቸው ተያይዞ የቀረበበት ምንባብ ነው፡፡ በሃሳብ ቀላልነት ደረጃም በምዕራፍ 1.2 እና 5 ያሉት ምንባቦች ቀላል ናቸው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

መ2. ግልፅ ሃሳብ የያዙ በርካታ ምንባቦች በመፅሃፉ ውስጥ አሉ፡፡ ለምሳሌ ሳይንስና ቴክኖሎጅ የሚለው ምንባብ አሻሚ ሃሳብ የለውም፡፡ ስለየአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች፣ ስለየተራቆተን አካባቢ ማልማት የሚዳሱት ምንባቦች ቀላል ሃሳብ የያዙ ናቸው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ስለባህል የሚያወራው ተበቺሳ የሚለው ምንባብ ለመረዳት የሚያስቸግር ይመስለኛል፡፡

መ3. እና መ.4 ሁሉም ምንባቦች የሃሳብ ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች አቅርበዋል፡፡ ነገር ግን እኩል ስፋትና ጥበት ባይኖራቸውም የሚያቀርቡሃሳብ ቀላልና ግልፅ ናቸው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

መ5. እናመ6. አብዛኛዎቹ ምንባቦች ቀላልና ግልፅ ሃሳብ የሚያቀርቡ ቢሆንም እናቲቱ የሚለው ልቦለድ ግን ከባድ ሃሳብ ይዟል የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡

4.3. የጥናቱ የውጤት ማብራሪያ

የጥናቱ የመጀመሪያው ዝርዝር ዓላማ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ወቅታዊነት መፈተሽ የሚል ነበር፡፡ ምንባቦቹን ከወቅታዊነት አንፃር ለመፈተሽ ከሰነድ ፍተሻና ከቃለመጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበው በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ተተንትነዋል፡፡ በሰነድ ፍተሻውና በቃለመጠይቁ ከተገኙ የመረጃ ትንተና በመፅሃፉ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ወቅታዊነት እንዳላቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ምንባቦቹ፣ ወቅታዊነት ያላቸው ሆነው ተገቢ እንደሆኑና እንዳልሆኑ ለመፈተሽ በምዕራፍ 2 በክለሳ ድርሳን የተገለፁ መመዘኛ መስፈርቶች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በመስፈርቶቹም መሰረት ጥናቱ የደረሰበት ውጤት ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

በምዕራፍ 1፣ በምዕራፍ 2፣ በምዕራፍ 4፣ በምዕራፍ 5፣ በምዕራፍ 6፣ በምዕራፍ 8፣ በምዕራፍ 9፣ እና በምዕራፍ 10 ስር የቀረቡት ምንባቦች ከወቅታዊነት አኳያ ተገቢ ምንባቦች እንደሆኑ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ በምዕራፍ 1 ስር የቀረበው ባህላዊ ሽምግልና የሚለው ምንባብ፣ ሃሳቡ ስለየሽምግልና ስርዓት የሚዳስና ተማሪዎች ሃሳቡን በአካባቢያቸው ካለው የማህበረሰብ መስተጋብር የሚያጤኑት ጉዳይ ነው፡፡ በምዕራፍ 2 የሽማግሌው ምርቃት የሚለው ምንባብ፣ የሽማግሌ የምርቃት በረከትን ተማሪዎች ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ህይዎት ጋር አያይዘው የሚረዱት ነው፡፡ በምዕራፍ 4 ወረርሽና ስነልቦናዊ ምላሾች የሚለው ምንባብ ወረርሽን አስከፊ፣ ህይዎት የሚቀጥፍና በፍተኛ ቁጥር ለህልፈት የሚዳርግ መሆኑም ስነልቦናዊ ተፅዕኖ አድራሽ እንደሆነ ተማሪዎች ካለፉበት ህይዎት የሚረዱት፣ በአካባቢያቸው የሚያጤኑትና አዲስ ያልሆነ ጉዳያቸው ነው፡፡ በቀሪዎቹ ምዕራፎች ስር የሚገኙት ምንባቦች ከዚህ ገለፃ ያልተለዩ ወቅታዊ ምንባቦች ናቸው፡፡ጉዳዩም የምንባቦቹ ይዘት ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ሁነት ጋር እንዲያይዙ የሚጋብዙ፣ ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋር የተቀራረቡ ጉዳዮችን የሚያንፀባርቁ ምንባቦች ወቅታዊነት እንዳላቸው በGuba and Lincoln (1989) እና በKramsch (1993) ከተገለፁ ሃሳቦች ጋር ተደጋጋፊነት አለው፡፡

ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በመገናዘብና ባህላዊ ክንዋኔዎችን በመግለፅ በምዕራፍ 3 ስር የቀረበው ሳይንስና ቴክኖሎጅ ለዘላቂ ልማት የሚለው ምንባብ እና በምዕራፍ 7 ስር የሚገኘው ተበቺሳ የሚለው ምንባብ ወቅታዊነት ያላቸውምንባቦች እንደሆኑ የጥናቱ ውጤት ጠቁሟል፡፡ በምዕራፍ 3 የቀረበው ሳይንስና ቴክኖሎጅ ለዘላቂ ልማት የሚለው ምንባብ ሳይንስ ለቴክኖሎጅ ፈጠራ አስፈላጊ እንደሆነ የሚያወሳ ነው፡፡ ብዙ የቴክኖሎጅ ውጤቶችን እየተጠቀምንባቸው እንዳለግልፅ ነው፡፡

ለምሳሌ ግብርናውን አዘምነን የምንጠቀምባቸው መሳሪያዎች፣ በእጆቻችን የያዝናቸው ስልኮች ሳይንስ የፈጠራቸው የቴክኖሎጅ ውጤቶች ናቸው፡፡ እነዚህን ቋቡሎች የሚገልፅ ምንባብ ደግሞ ሃሳቡ ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ይህም ሃሳብ ወቅታዊነት እንዳለው አብነት በመሆኑ ምንባቡ ወቅታዊ ጉዳይን ዳሷል ወደሚል ድምዳሜ አድርሷል፡፡ በምዕራፍ 7 ተበቺሳ በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ የደቡብ ወሎ የለሚ አካባቢ ወጣቶች ፍቅራቸውን የሚገልፅባቸውን የተበቺሳን ባህል ይገልፃል፡፡ ምንባቡ የአሁኑ ወጣት ፍቅራቸውን ሊገልፅበት የሚችለውን ሁነት፣ አጋጣሚ ገላጭ በመሆኑ ወቅታዊ ነው፡፡

ጉዳዩም የምንባቦቹ ይዘት ከወቅቱ የሃገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ሲገናዘቡ፣ ባህላዊ ክንዋኔዎችን የሚገልፁ ሆነው ሲገኙ ወቅታዊነት እንዳላቸው በGuba and Lincoln (1989) እና በKramsch (1993) ከተገለፁ ሃሳቦች ጋር ተደጋጋፊነት ያለው ሆኗል፡፡

ሁለተኛው ዓላማ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ግልጽነት መፈተሽ የሚል ነበር፡፡ ከግልፅነት አንፃር በምዕራፍ 6፣ በምዕራፍ 8 እና በምዕራፍ 10 ስር የቀረቡት ምንባቦች የኢመደበኛ ቃላት አጠቃቀም ችግር ስለማይታይባቸው የግልፅነት ችግር እንደሌለባው የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በምዕራፍ 1፣ በምዕራፍ 2፣ በምዕራፍ 3፣ በምዕራፍ 4 እና በምዕራፍ 5 ስር የቀረቡት አምስት ምንባቦች ደግሞ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ከባድ ቃላት፣ የዘየ ቃላትና የሙያ ቃላት እንደ ተካተቱባቸው መረዳት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጅ ኢመደበኛ ቃላቱ አነስተኛ በመሆኑ የጎላ የግልፅነት ችግር የለባቸውም፡፡ በምዕራፍ 7 ተበቺሳ የሚለው ምንባብና በምዕራፍ 9 እናቲቱ የሚለው ምንባብ በርካታ ቁጥር ባላቸው ዘየ፣ የሙያ፣ ከባድና ፈሊጣዊ ቃላት የተደረሰ በመሆናቸው ግልፅነቱን የሚያጓድሉ ኢመደበኛ የቃላት አጠቃቀም ችግር ያለባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ጉዳዩም የቃላት አጠቃቀማቸው ተገቢነት የሌላቸው፣ በርካታ ኢመደበኛ ቃላትን ያካተቱ ምንባቦች የግልፅነት ችግር የሚነሳባቸው እንደሆኑ በCummins (2017) እና በArias (2007) ከተገለፁ ሃሳቦች ጋር ተደጋጋፊነት ያለው ነው፡፡

ሌላው የምንባቦቹን ግልፅነት ለመፈተሽ የተተኮረበት ጉዳይ ምንባቦቹ በቀላሉ ተነበው ሊረዷቸው የሚችሉ መሆን አለመሆናቸውን በመፈተሽ ነው፡፡ በሰነድ ፍተሻና በቃለመጠይቅ ከተገኙ መረጃዎች ማረጋገጥ እንደሚቻለው በምዕራፍ7 እና በምዕራፍ9 ስር የቀረቡት ምንባቦችሃሳባቸውን ለመረዳት የሚከብዱ፣ለክብደቱ መንስኤም የዘየ፣ የሙያ፣ ከባድና የፈሊጣዊ ቃላት የተካተተባቸው ምንባቦች በመሆናቸው ነው፡፡ ስለሆነም አንብበው ለመረዳት የሚከብዱ እንደሆኑ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡

ጉዳዩም በምንባብ ውስጥ የቀረቡትን ሃሳቦች ተማሪዎች በቀላሉ አንብበው የሚረዷቸው ሆነው ሲገኙ ግልፅነት ያላቸው ምንባቦች እንደሆኑ በCummins (2017)፣ በTaylor (2004) እና በGlodbery (2007) ከተገለፁ ሃሳቦች ጋር የተቃረነ ሁኗል፡፡

ሶስተኛው ዓላማ ደግሞ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ተነባቢነት መፈተሽ የሚል ነው፡፡ ከተነባቢነት አንፃር ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ አስር ድረስ የቀረቡትን ምንባቦች በሰነድ ፍተሻና በቃለ መጠይቅ ለመፈተሽ የተተኮረባቸው ጉዳዮች የምንባቦቹ አረፍተ ነገር አመሰራረት፣ የምንባቦቹ የቃላት አጠቃቀምና የምንባቦቹ ሃሳብ የቀላልነትና የግልፅነት ጉዳይ ነበር፡፡ ሆኖም ጥናቱ ከቃላት አጠቃቀም አንፃር፣ ከሃሳብ ቀላልነትና ግልፅነት በምዕራፍ 7 እና 9 ስር የቀረቡት ምንባቦች በርካታ ኢ መደበኛ ቃላት እንደ ተካተቱባቸው አመልክቷል፡፡ ከምንባቦቹ አረፍተ ነገር አመሰራረት አንፃር በብዙ ቀጥር ባላቸው ውስብስብ አረፍተ ነገሮች የተደረሱት በምዕራፍ 1 እና በምዕራፍ 9 ስር የቀረቡት ምንባቦች እንደሆኑ የጥናቱ ውጤት ጠቁሟል፡፡ ይህም ምንባቦች ነጠላና ግልፅ አረፍተ ነገሮችን ካልያዙ፣ ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን በብዛት ካልተጠቀሙ፣ የቃላት አጠቃቀማቸው መደበኛ ከሆኑ ተነባቢነት ያላቸው ምንባቦች እንደሆኑ በWilliam (2004) Strunk (1959) and Joseph (1990) ከተገለፁት ሃሳቦች ጋር የሚቃረን ሆኗል፡፡

ምዕራፍ አምስት፡-ማጠቃለያ መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳብ

5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2015 ዓ.ም. በታተመው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ምንባቦች ተገቢነት መፈተሽ ነው። ይህን ዓላማ ለማሳካት በመሳሪያዎች ፍተሻ የተገኙት ውጤቶች ቀጥሎ ቀርቧል፡፡ መስፈርቶቹም የምንባቦቹ ይዘት ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘቡ እንደሆኑ፣ የምንባቦቹን ይዘት ከአካባቢያቸው ሁነት ጋር እንዲያይዙ ጋባዥ እንደ ሆኑ፣ ባህላዊ ክንዋኔዎችን የሚገልፁ ምንባቦችና ተማሪዎች ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋር የተቀራረቡ ጉዳዮችን የሚገልፁ ነበሩ፡፡ የእነዚህን መስፈርቶች ሃሳብ መነሻ በማድረግ በዓላማ አንድ መሰረት በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ያላቸውን ወቅታዊነት መፈተሽ ነበር፡፡ ከወቅታዊነት አንፃርም በመፅሃፉ ውስጥ ያሉት ሁሉም አስሩም ምንባቦች ከወቅቱ አኳያ ሁሉም ምንባቦች ተገቢ እንደ ሆኑ ከሰነድ ፍተሻው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሰነድ ፍተሻውም ሆነ በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚያመላክተው የምንባቦቹ ይዘት ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘቡና ተገቢ መሆናቸው፣ የምንባቦቹን ይዘት ከአካባቢያቸው ሁነት ጋር እንዲያይዙ መጋበዛቸው፣ በምዕራፍ አንድ፣ ሁለት፣ አራት፣ ስድስትና ስምንት ስር የሚገኙ ምንባቦችም መጥቀስ እንደሚቻል፣ ባህላዊ ክንዋኔዎችን የሚገልፅ በምዕራፍ ሶስት የሚገኘው ምንባብ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሁለተኛው ዓላማ መሰረት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ግልጽነት ያላቸው መሆናቸውን መፈተሽ ነበር፡፡ ከሰነድ ፍተሻውና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው ከቃላት አጠቃቀም አንፃር ተገቢነት ያላቸው፣ ምንም አይነት የኢመደበኛ ቃላት ችግር የሌላቸው በምዕራፍ 6፣ በምዕራፍ 8 እና በምዕራፍ 10 ስር የሚገኙት ምንባቦች እንደ ሆኑ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በምዕራፍ 7 እና በምዕራፍ 9 ስር የቀረቡት ምንባቦች ዘየ፣ ከባድ ፈሊጦች የበዙባቸው፣ ተገቢነታቸው የተጓደሉ ምንባቦች እንደሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡ ከእነዚህ ምንባቦች ውጭ ያሉ አምስት ምንባቦች ማለትም በምዕራፍ 1፣ በምዕራፍ 2፣ በምዕራፍ 3፣ በምዕራፍ 4፣ እና በምዕራፍ 5 ስር የሚገኙት ምንባቦች ደግሞ የኢመደበኛ ቃላት አጠቃቀም በመጠኑ የታየባቸውና ለተገቢነት ችግር አጋላጭ እንዳልሆኑ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የምንባቦቹ ግልጽነት ለመመርመር የተተኮረበት ሌላው ነጥብ በቀላሉ ተነበው መረዳት የሚችሏቸው መሆናቸውን በመፈተሽ ነበር፡፡ ከጥናቱ ውጤት ማጤን እንደ ተቻለውም በምዕራፍ 7 እና 9 የቀረቡት ምንባቦች ከባድ እንደሆኑ፣ ለክብደቱ መንስኤም የዘየ፣ የሙያ፣ ከባድና የፈሊጣዊ ቃላትን አብዝቶ መጠቀም ይህም ምንባቦቹን ለመረዳት ግልፅነቱን የሚያጓድሉ እንደሆኑ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡

በዚህ ጥናት በሶስተኛው ደረጃ የተገመገመው ሌላው ጉዳይ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ተነባቢነት የተመለከተ ነው፡፡ ከሰነድ ፍተሻውና ከቃለ መጠይቁ መረጃ ማረጋገጥ እንደተቻለው በምዕራፍ 1 እና በምዕራፍ 9 ስር የቀረቡት ምንባቦች በብዙ ቀጥር ባላቸው ውስብስብ አረፍተ ነገሮች የተደረሱት ምንባቦች እንደሆኑ፣ ከዚህ ውጭ ያሉት ደግሞ በብዙ ነጠላ አረፍተ ነገሮች የቀረቡና ግልፅነት ያላቸው ምንባቦች እንደ ሆኑ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ ሌላው የምንባቦቹን ተነባቢነት ለመገምገም የተተኮረበት ነጥብ የምንባቦቹ ሃሳብ የቀላልነትና የግልፅነትን የተመለከተ ነበር፡፡ የጥናቱ ውጤት እንዳመላከተውም መማሪያ መፅሃፉ ውስጥ የቀረቡት ሁለት ምንባቦች ለመረዳት ከባድ ሃሳብ የያዙ እንዳሉ ሁሉ፣ ስምንት ምንባቦች ደግሞ ለመረዳት ቀላልና ተገቢ እንደሆኑ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

5.2 መደምደሚያ

በዚህ ጥናት በ2015 ዓም በታተመው በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ያላቸው ተገቢነት በተለያዩ መስፈርቶች ተፈትሸዋል፡፡

- ✓ በመማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉት ምንባቦች፣ ከወቅታዊነት አንፃር ሲፈተሹ፣ ወቅታዊነት ያላቸው ተገቢ ምንባቦች እንደሆኑ ጠቋሚ ፍንጮች እንዳሉ የጥናቱ ውጤት ጠቁሟል፡፡ ለወቅታዊነታቸው ማሳያም ሁሉም ምንባቦች ከወቅቱ ተጨባጭ ሁነት ጋር ቁርኝት ያላቸው መሆናቸው፣ በምዕራፍ 7 ተበቺሳ የሚለው ምንባብ ባህላዊ ክንዋኔን የሚገልፅ መሆኑ፣ በምዕራፍ 1፣ በምዕራፍ 2፣ በምዕራፍ 4፣ በምዕራፍ 5፣ በምዕራፍ 6፣ በምዕራፍ 8፣ በምዕራፍ 9፣ እና በምዕራፍ 10 ስር የቀረቡት ምንባቦች ይዘታቸው ተማሪዎች ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ህይዎት ጋር ግንኙነት ያላቸውና፣ አካባቢያዊ ሁነቶችን መነሻ ያደረጉ መሆናቸው ወቅታዊነት ያላቸው ተገቢነት ምንባቦች ሆነው ተገኝተዋል፡፡

- ✓ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ግልጽነት ያላቸው ከመሆናቸው አንፃር ሲፈተሹ ሶስት ምንባቦች የቃላት አጠቃቀማቸው መደበኛ የሆኑ፣ ሁለት ምንባቦች ደግሞ የቃላት አጠቃቀም ችግር ያለባቸው ሆነዋል፡፡ ተማሪዎች ሃሳቡን ለመረዳት የማይከብዱ ሰባት ምንባቦች፣ ለመረዳት የሚከብዱና ፈታኝ ሃሳብ የያዙ ደግሞ ሁለት ምንባቦች ተካተው ተገኝተዋል፡፡
- ✓ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ተነባቢ ከመሆናቸው አንፃር ሲፈተሹ በምዕራፍ 1 እና በምዕራፍ 9 ስር በቀረቡት ምንባቦች ስር የሚገኙ ብዙዎቹ ዐረፍተ ነገሮች ውስብስብ እንደሆኑ፣ ተማሪዎች በቀላሉ በማይረዷቸው መንገድ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ምዕራፎች ውጭ ያሉት ምንባቦች ግን በአብዛኛው በነጠላ አረፍተ ነገሮች የተገነቡ ሆነው የቀረቡ ናቸው፡፡ ከሃሳብ ግልፅነትና ቀላልነት አንፃር ደግሞ የሁሉም ምንባቦች ሃሳብ በደንብ የተደራጁ፣ ተያያዥነት ያላቸውን ሃሳቦች የሚያቀርቡ ተገቢ ምንባቦች እንደሆኑ ከጥናቱ ውጤት መረዳት ተችሏል፡፡

5.3 አስተያየት

ከመረጃዎቹ የተገኙትን ውጤቶች መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን አስተያየቶች አጥኝው አቅርቧል፡፡

- ➢ **ለተማሪዎች፡-** የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚያስችሉ፣ የገሃዱን አለም እንዲገነዘቡ የሚያስችሉ፣ የአስተሳሰብ አድማሳቸውን እንዲያሰፉ የሚያግዙ፣ ወቅታዊ፣ ተነባቢነትና ግልፅነት ያላቸው ምንባቦች ቢቀርባላቸው፤
- ➢ **ለመፅሃፍት አዘጋጆች፡-** በመማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የተካተቱ ምንባቦች ወቅታዊነት እንዳላቸው በተለያዩ መመዘኛዎች ሲመገሙ ለክፍል ደረጃው ተገቢ የሆኑ ምንባቦች እንደተካተቱ በሰነድ ፍተሻ፣ በቃለ መጠይቅ በተገኘው ተደጋጋፊ መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡ ስለሆነም በመማሪያ መፅሃፍት ውስጥ የሚካተቱ ምንባቦች ለክፍል ደረጃው ተማሪዎች ተገቢ እንዲሆኑ ያለው አካሄድ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡ የተማሪዎችን፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚያስችሉ በብዙ መልኩ ተገቢ የሆኑ ምንባቦች የበለጠ ተሰናድቶ በመፅሃፍት አዘጋጆች ቢቀርብላቸው፤

- ➢ **ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፡-**በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉ ምንባቦች ተገቢነት እንዳላቸውና እንደሌላቸው የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ስለሚያግዝ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚያስችሉ ምንባቦችን ለማቅረብ አጋዥ ሃሳብ ሊሰጥ ይችላል፡፡
- ➢ **ለተመራማሪዎች፡-**በምንባብ ተገቢነት ዙሪያ ጥናት ለሚያካሂዱ ሰዎች እንደ መነሻ ሆኖ እንደ መነሻ ቢጠቀሙበት ውጤታማ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ዋቢዎች

መአዛ አብርሃ፡፡ (2009)፡፡ “ተፍታሽ ምንባባት ትግርኛ መፅሃፍ ተምሃራይ 11ክፍሊ ንምምሃር ክእለት ንባብ ዘለዎም ግቡእነት፡፡” ንመማልኢ ካልአይ ዲግሪ ብምስትምሃር ቋንቋ ትግርኛ ዝቐረበ መፅናእታዊ ፅሁፍ፡፡ መቐለ ዩኒቨርሲቲ፣ (ዘይትሓተመ)፡፡

መጋቢው ኃይለማርያም፡፡ (2009)፡፡ “በ2004 ዓ.ም በተዘጋጀው የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦች የተነባቢነት ደረጃ፡፡” በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ (ያልታተመ)፡፡

ሙሉ ገበያው፡፡ (2009) ፡፡ **የፅሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና፡፡** በአድ ስአበባ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፣ (ያልታተመ)፡፡

ስዩም ከበደና ሌሎች፡፡ (1994)፡፡ **አማርኛ የማስተማር ስነዘዴ፡፡** አዲስ አበባ፣ ትምህርት ሚኒስቴር፡፡

ተስፋዬ ሽዋየ፡፡ (1981)፡፡ **በስነ ልሳን ቋንቋን ማስተማር፡፡** አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የማነ ገብረፃዲቅ፡፡ (2009)፡፡ “በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦች የመቀበያ ክሂሎችን ለማስተማር ያላቸው ተገቢነት።” በተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሑፍ፡፡ መቐለ ዩኒቨርሲቲ፣ (ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ። (2009) ፡፡ **የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር።** ባህርዳር፣ ተፈሪ ስዩም ማተሚያ ድርጅት።

Apple, M. W., & Christian-Smith, L. K. (Eds.). (1991). **The politics of the textbook**. Routledge.

Arslan, S. (2016). An analysis of a coursebook: Does it smell Turkish? Educational Sciences: Theory & Practice, 16 (4), 1357-1376.

Byrd,P.(2001). **Textbook Evaluation and Selection**. 3rd ed. Boston: Heinle & Heinle

Carrell, P. L. (2006).**Can Reading Strategies be Successfully Taught**.The Language Teacher Journal. JALT N22/

Cunningsworth, A. (1995).**Choosing your coursebook**.London. Heinermann Educational books.

Cummins,J,(2017), **language and learning: simplification and Vocabulary in educational texts.** USA. University of Chicago press.

Day,R.R(1994). Selecting a passage for the EFL readindg class.Forum. 32.2;20-23

.Desalegn, T. (2018).**Cultural representation in the Grade 11 English language textbook in Ethiopia.**[Unpublished master's thesis].Addis Ababa University.

Dubin and Olshtain.(1988). **Course Design Developing Programs Materials or Language Learning.** Cambridge: Cambride University Press.

Flesch, R. (1946). **The art of readable writing**. USA. Harper and Brothers.

Goldberg, Kathy. (2007). **Conferring with Readers**: Supporting Each Students Growth and Independence.

Grant, N. (1987) **Making The Most of Your Text Book**. NewYork: Harper and Brothers.

Gizaw, M. (2020). An evaluation of reading comprehension activities in the Grade 7 English textbook. Ethiopian Journal of Education, 40 (1), 85-104.

Hutchinson, T., & Torres, E. (1994).**The textbook as agent of change**.ELT Journal, 48(4), 315–328.

Joseph,M. Williams,(1990). **Style: Towards Clarity and Grace**. USA. University of Chicago press.

Khemlani,D.(2004). **Selection of Reading Text**: Moving Beyond Context Schama.

Kifle Adera. (2009). **Ashort cut to Curriculum Designing, planning, Development and Implementation.** Addis Ababa, Artistic Printin Enterprise.

Kramsch,C.(1993). **Context and Culture in Language Teaching**.Oxford University of

Krashen, S. D. (1985).**The input hypothesis**: Issues and implications. Longman.

Krippendorff, K. (2018). **Content analysis: An introduction to its methodology** (4th ed.). Sage publications.

Lincoln, Y. S., & Guba, E. G. (1985).Naturalistic inquiry.Sage.

Mayer,R.E.(2009). **Multimedia Learning, Cambridege**. Cambridge university press,

Ministry of Education (MoE).(2022). **Amharic Language Student Textbook for Grade 9.** Federal Democratic Republic of Ethiopia.

Nuttal,C.(1982). **Teaching Reading Skills in Aforeign Language**. Oxford: Heinemann Educational Book Ltd.

Ndura, E. (2004). ESL and cultural bias: An analysis of elementary through high school textbooks in the Western United States of America. Language, Culture and Curriculum, 17(2), 143-153.

Strunk,W and White,E,B,(1959), **The Elements Of Stayle**.USA. person education.

.Tomlinson, B. (Ed.). (2011). **Materials development in language teaching** (2nd ed.). Cambridge University Press.

Richards, J.C. and Schimidt,R.(2002). **Longman Dictionary of Language Teaching & Applied Linguistics.**3rd Edition. London: Pearson Education.

Routman, R.(2000). **Strategies for Teaching Learning and Evaluating**. Protsmouth,NH: Heinemann.

Serafini,F. (2001).**The Reading Workshop:** Creating Space for Reader. Portsmouth.

Taylor,R.(2014). **Coherence and Organization in educational materials**.USA. University of Chicago press.

Weaver, frank.(2002). **Reading Process and Practice**. 3rd Edition Portsmouth.

William,K.(2014). **Writing as thinking correspondence Essays**. USA. Harvard university press.

አባሪዎች

አባሪ ‹ሀ› ለመምህራን የሚቀርብ የቃለ-መጠይቅ ጥያቄዎች

መቐለ ዩኒቨርሲቲ

የህብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል (አማርኛ)

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረቡ ቃለ መጠይቆች

ይህ ቃለ መጠይቅ በመቐሌ ዩኒቨርሲቲ ለ2ኛ ዲግሪ መመረቂያ ፅሁፍ መሟያነት በሓጎስ ስብሃቱ የጥናት ርዕስ በ2015 ዓ.ም በተዘጋጀው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሓፍ የቀረቡ ምንባቦች ተገቢነት ግምገማ›› በሚል ርዕስ በቃለ መጠይቅ ለመረጃ መሰብሰቢያ የተዘጋጀ ነው፡፡ በቃለመጠይቁ የቀረቡ ሃሳቦችንም በጥንቃቄ በማዳመጥ ቃላዊ ማብራሪያ ሰጡ፡፡

የምንባቦቹን ተገቢነት መፈተሻ የቃለ-መጠይቅ ጥያቄዎች

1.በ2015 ዓ.ም በተዘጋጀው የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ናቸው ብለው ያምናሉ ምሳሌ ቢጠቅሱ2.በ2015 ዓ.ም በተዘጋጀው የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች፣ ይዘት ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ሁነት ጋር እንዲያይዙ የሚያደርጉ ናቸው ምሳሌ ቢጠቅሱ

3. በተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ባህላዊ ክንዋኔዎችን የሚገልፁ፣ ተማሪዎች ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋር የተቀራረቡ ጉዳዮችን የሚያንፀባርቁ ምንባቦች ቀርበዋል ብለው ያስባሉ ለምሳሌ

4. በዘጠንኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ምክንያታዊ የሆነ የሃሳብ ተያያዥነት ያላቸው፣ ሊተላለፍ የተፈለገን ጉዳይ በደንብ የገለፁ ናቸው ብለው ያስባሉ? ምሳሌ ቢጠቅሱ

5. በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ተማሪዎች ሊረዷቸው በሚችሉት መደበኛ ቃላት የቀረቡ ናቸው እንዴት

6. በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች በቀላሉ በሚረዷቸው አረፍተ ነገሮች ተገንብተዋል አረፍተ ነገሮቹስ የሃሳብ ተያያዥነት ያላቸውን ሃሳቦች ይገልፃሉ

7. በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች የቋንቋ አጠቃቀማቸው (ከሰዋሰው ስህተትና ከቋንቋ አጠቃቀም ችግር) አንፃር ግልፅነት አላቸውን ምሳሌ ቢጠቅሱ

አባሪ ‹ለ›በቃለ መጠይቅ የተመረጡ የመምህራን ዳራዊ መረጃ

መምህር	የሚያስተምሩበት ት/ቤት	የሚያስተምሩት የትምህርት አይነት	የስራልምድ	ፆታ
መ 1	በወልዋሎ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት	አማርኛ	15 ዓመት	ወ
መ 2	በወልዋሎ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት	አማርኛ	18 ዓመት	ወ
መ 3	በወልዋሎ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት	አማርኛ	14 ዓመት	ወ
መ 4	በወልዋሎ 2ኛደረጃ ትምህርት ቤት	አማርኛ	18 ዓመት	ወ
መ 5	በወልዋሎ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት	አማርኛ	13 ዓመት	ወ
መ 6	በወልዋሎ 2ኛደረጃ ትምህርት ቤት	አማርኛ	19 ዓመት	ወ

አባሪ. ‹ሐ› በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች መረጃ

ምዕራፎችና ምንባቦች	አጠቃላይ የአረፍተ ነገሮችብዛት	የነጠላ የአረፍ ተነገሮች ብዛት	በመቶኛ	የውስብስብ የአረፍተ ነገሮች ብዛት	በመቶኛ
ምዕራፍ 1 ባህላዊ ሽምግልና	45	17	37.7%	28	62.3%
ምዕራፍ 2 የሽማግሌው ምርቃት	103	73	70.9%	30	29.1%
ምዕራፍ 3 ሳይንስና ቴክኖሎጂ	39	22	56.4%	17	43.6%
ምዕራፍ4 ወረርሽኝና ስነልቦናዊ ምላሾች	52	27	51.9%	25	48.9%
ምዕራፍ 5 ፀሀይና ተግዳሮቶቿ	49	28	57.1%	21	42.9%
ምዕራፍ 6 የተራቆተን አካባቢ ማልማት	45	28	62.2%	17	37.8%
በምዕራፍ 7 ተበቺሳ	55	29	52.7%	26	47.8%
ምዕራፍ 8 ግብር መክፈል	34	16	47.1%	18	52.9%
ምዕራፍ 9 እናቲቱ	144	59	40.9%	85	59.1%
ምዕራፍ 10 የልማት አርበኛው ጀኔራል	40	25	62.5%	15	37.5%

አባሪ ‹መ› አማርኛ ቋንቋ ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ የቃለ-መጠይቅ ምልልሶች ቅጅ

መቐለ ዩኒቨርሲቲ

የህብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል (አማርኛ)

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለስድስት መምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ የተካሄደበት ቀንና የስዓት መረጃ

ቀን 10/10/17 ዓም

የትምህርት ቤቱ ስም ወልዋሎ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

ስዓት 2፡00-4፡20

1.በ2015 ዓ.ም በተዘጋጀው የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ከወቅቱ ተጨባጭ ሁነት የተገናዘቡ ናቸው ብለው ያምናሉ? ምሳሌ ቢጠቅሱ?

መ1. በእኔ አስተያየት ምንባቦቹ ወቅታዊ እንዲሆኑ ጥረት የተደረገባቸውናቸው፡፡ በቅርብ ህትመት ላይ የተመሰረቱ፣ በተፃፉበት ወቅት ያለውን ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ገፅታ ማቅረባቸው ወቅታዊ ናቸው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡ ለምሳሌ በምዕራፍ1 ባህላዊ ሽምግልና የሚለው ምንባብ ከሚዳሰው ሃሳብ ማህበራዊ ጉዳይ አንዱበመሆኑ፣ ባለንበት የአካባቢ አውድ የቀረቡ መሆናቸው የወቅታዊነቱ መገለጫ ነው ባይ ነኝ፡፡

መ2. ምንባቦቹ ወቅታዊ ናቸው፤ የሚያነሱት ጭብጥ ለህይዎታችን ቅርብ፣ ለማህበራዊ ህይዎታችን ጋር የተቆራኙ፣ በቅርብ ዓመታት የታተሙ በመሆናቸው ወቅታዊ ናቸው የሚልሃሳብ አለኝ የሚል ሃሳብ የሰጠ በመሆኑ ከመምህር አንድ ሃሳብ የተቀራረበ አስተያየት ሰጥቷል፡፡

መ3. ተበቺሳ ከሚለው ባህል አስተዋዋቂ ምንባብና እናቲቱ ከሚለው የልቦለድ ምንባብ ውጭ ያሉት ተማሪዎቹ በቀላሉ የሚረዷቸው ናቸው፡፡ የሚያነሱት ሃሳብም የሃገራችንን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ነው፡፡ ከዚህም አንፃር ወቅታዊ ናቸው የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡

መ4. ምንባቦቹ የቅረብ ክስተቶችን የሚያቀርቡ መሆናቸው የወቅታዊነታቸው ማሳያ ግምንባቦች የቅርብ ጉዳይ፣ በተጨባጭ ገሃዱ አለም ላይ ያሉ ጉዳዩችን ማቅረባቸው ወቅታዊ ናቸው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡ በምንባቦቹ በኢትዮጵያዊን ደራሲዎች በቅርብ ዓመታት መታተማቸው እንዲሁ የወቅታዊነት ማሳያቸው ነው፡፡

መ5.በእኔ አስተያየት ምንባቦቹ ወቅታዊ እንዲሆኑ ጥረት የተደረገባቸው ናቸው፡፡ በቅርብ ህትመት ላይ የተመሰረቱ፣ በተፃፉበት ወቅት ያለውን ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ገፅታ ማቅረባቸው ወቅታዊ ናቸው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡ ለምሳሌ በምዕራፍ1 ባህላዊ ሽምግልና የሚለው ምንባብ ከሚዳሰው ሃሳብ ማህበራዊ ጉዳይ አንዱ በመሆኑ፣ ባለንበት የአካባቢ አውድ የቀረቡ መሆናቸው የወቅታዊነቱ መገለጫ ነው ባይ ነኝ፡፡

መ6. ተበቺሳ ከሚለው ባህል አስተዋዋቂ ምንባብ ውጭ ያሉት ምንባቦች ተማሪዎቹ በቀላሉ የሚረዷቸው፣ የሃገራችንን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ማቅረባቸው ወቅታዊ እንደሆኑ ያሳያል የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡

ቀን 11/10/17 ዓም

የትምህርት ቤቱ ስም ወልዋሎ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

ስዓት 2፡00-4፡00

2.በ2015 ዓ.ም በተዘጋጀው የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች፣ ይዘት ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ሁነት ጋር እንዲተዋወቁ የሚያደርጉ ናቸው? ምሳሌ ቢጠቅሱ?

መ1. እና መ3. ምንባቦቹ በአካባቢ ካሉ ክስተቶች፣ ጉዳዮች ጋር ቁርኝት አላቸው፡፡ የሽምግልና ስርዓትን የሚያወሳው ምንባብ በአካባቢ ካሉ የሽምግልና ስርዓት ጋር ግንኙነት አለው፡፡ የሽማግሌው ምርቃት የሚለው ምንባብ ምርቃት የሚያደርሱ አዛውንቶች(ሰዎች) በተለያየ አጋጣሚ ሰዎችን ሲመርቁ ከሚያዩት ድርጊት ጋር ግንኙነት አለው፡፡ የሁሉም ምንባቦች ሃሳብ ሲፈተሽ ተማሪዎቹ ከሚኖሩበት የአካባቢ ባህል፣ ድርጊት ወዘተ ጋር ቁርኝት እንዳላቸው ይገልፃሉ የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

መ2. የምንባቦቹን ሃሳብ ለመረዳት ከገሃዱ ዓለም ወይን ከአካባቢያቸው ሁነት ጋር ማያያዝ ተገቢነት አለው፡፡ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ደግሞ ከገሃዱ አለምና ከአካባቢው ሁነት ጋር አያይዘው

እንዲረዷቸው ይጋብዛሉ፡፡ ስለልማት አርበኛው የሚገልፀው ምንባብ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ጠንካራ ሰራተኛ ከሆኑ ሰዎች ህይዎት ጋር እንዲያይይዙ ይጋብዛል፡፡

መ3. ምንባቦቹ ከአካባቢያዊ ሁነቶች ጋር ሃሳባቸውን አያይዘው እንዲረዷቸው ይጋብዛሉ፡፡ ለምሳሌ የልማት አርበኛ የሚለው ምንባብ በአካባቢ ካሉ ንቁ የልማት ሰራተኞች ጋር አያይዘው እንዲረዱት ይጋብዛል፡፡

መ5. ምንባቦቹ የሚያነሷቸው ሃሳቦች ከአካባቢያቸው አውድ ጋር ግንኙነት ያላቸው በመሆናቸው ሃሳባቸውን ለመረዳት አጋዥ ዳራ እንዳላቸው አስተያየት ሃሳብ ሰጥቷል፡፡

መ6. ምንባቦቹ የሚያነሷቸው ሃሳቦች ከአካባቢያቸው አውድ ጋር ግንኙነት እንዳላቸው፣ ሃሳባቸውንም ለመረዳት የሚረዳ የመነሻ ዳራ እንዳላቸው ተቀራራቢ ሃሳብ ሆኗል፡፡

ቀን 11/10/17 ዓም

የትምህርት ቤቱ ስም ወልዋሎ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

ስዓት 8፡00-11፤00

3. በተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ባህላዊ ክንዋኔዎችን የሚገልፁ፣ ተማሪዎች ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋር የተቀራረቡ ጉዳዮችን የሚያንፀባርቁ ምንባቦች ቀርበዋል ብለው ያስባሉ ለምሳሌ

የዚህ ጥያቄ ምላሽ ከጥያቄ2 ጋር ተመሳሳይ ሃሳብ ያለው በመሆኑ ደጋግሞ መጻፍ አላስፈለገም፡፡

ቀን 11/10/17 ዓም

የትምህርት ቤቱ ስም ወልዋሎ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

ስዓት 8፡00-11፤00

4. በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች የቃላት አጠቃቀማቸው ኢ መደበኛ ናቸውን?

መ1. መ2. በመፅሃፉ ውስጥ የሚገኙት ምንባቦች የቃላት አጠቃቀማቸው መደበኛ ቃላትን ተጠቅመዋል፡፡ ጥቂት ምንባቦች ላይ ግን፣ ሃሳባቸውን ለመረዳት በጣም አዳጋች ባይሆንም ኢመደበኛ ቃላትን የያዙ ምንባቦች አሉ፡፡

መ3. በምዕራፍ 6 እና በምዕራፍ 10 የቀረቡት ምንባቦች ከዘየ፣ ከሙያ እና ከአራዳ ቃላት የፅዱ ናቸው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ተበቺሳ የሚለው ምንባብ በርካታ ኢመደበኛ ቃላት አሉት የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

መ4. ምንባቦቹ በአብዛሃኛው አስረጅ ድርሰቶች ናቸው፡፡ሲፃፉም የቃላት አጠቃቀቸው መደበኛ ለማድረግ ጥረት እንደተደረገ ምሳሌ የሚሆኑ ምንባቦች አሉ፡፡ ለምሳሌ የልማት አርበኛው፣ የሽማግሌው ምርቃት የሚሉት ምባቦች ከኢመደበኛ ቃላት የፀዱ ናቸው፡፡ ተበቺሳና እናቲቱ የሚሉት ምንባቦች በርካታ ዘየ፣ ፈሊጣዊና ከባድ ቃላትን ይዘዋል፡፡

መ5. እና መ6. ብዙዎቹ ምንባቦች የሃሳብ ግርታን በማይፈጥሩ፣ የተግባቦት ክፍተት በማያመጡ መደበኛ ቃላት የቀረቡ ናቸው፡፡ አንዳንድ ምንባቦች ደግሞ የሙያ ቃላትን ከተጠቀሙ ሳይንስና ቴክኖሎጅ የሚለው ምንባብ፣ ዘየቃላት ከተጠቀሙ እናቲቱ የሚሉት ምንባቦች ይጠቀሳሉ፡፡

ቀን 12/10/17 ዓም

የትምህርት ቤቱ ስም ወልዋሎ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

ስዓት 2፡00-4፡00

5.በዘጠንኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች የሃሳብ ውስብስብነት የሌላቸውና በቀላሉ አንብበው መረዳት የሚችሏቸው ምንባቦች ተመርጠዋል? ምሳሌ ቢጠቅሱ?

መ.1 በእኔ አስተያየት የብዙዎቹ ምንባቦች በቀላሉ አንብበው መረዳት የሚችሏቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ የምዕራፍ አንድ ምንባብ ስለሽምግልና ፋይዳ የሚያወሳ ነው፡፡ ይህ ተማሪዎች ባሉበት አካባቢ ሽማግሌዎች ሰዎችን ሲያስታርቁ የሚያዩት ቅርብ ጉዳያቸው ስለሆነ ለመረዳት ቀላል ነው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

መ.2 ዝርዝር ሃሳብ ለመስጠት ግን ሁሉንም ረጋ ብሎ ማንበብን የሚጠይቅ ቢሆንም ለአብነት ስለወረርሽኝ የቀረበው ምንባብ አንብበው መረዳት አይከብድም፡፡ ስለተበቺሳ የሚገልፅው ምንባብ ተማሪዎች ከሚያውቁት ባህል ጋር ግንኙነት አለው የሚያስብል አይመስለኝም፡፡ አንብበው መረዳት ከባድ ነው፡፡

መ.3 ስለ ሳይንስና ቴክኖሎጅ፣ ፅሃይና ተግዳሮቷ የሚገልፁት ምንባች አንብበው መረዳት ቀላል ናቸው፡፡ ምክንያቱም ለምሳሌ የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ተማሪዎች በትምህርታቸው የሚገጥማቸውን ችግር በአካባቢያቸው የሚታዘቡት ጉዳይ መሆኑ በቀላሉ አንብበው መረዳት ያግዛቸዋል የሚል ሃሳብ ሰጥቷል፡፡

ቀን 12/10/17 ዓም

የትምህርት ቤቱ ስም ወልዋሎ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

ስዓት 4፡00-3፡30

6. በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች አረፍተ ነገር አመሰራረታቸው ምን ይመስላል? በነጠላ ወይስ በውስብስብ አረፍተ ነገሮቹ የተመሰረቱ ናቸው ? ምሳሌ ቢጠቅሱ

መ1. እና መ2. ሁሉም ምንባቦች ነጠላና ውስብስብ አረፍተ ነገሮች አሏቸው፡፡ የትኛው እንደሚበዛ ግን ምንባቦች በእርጋታ ማንበብን ይጠይቃል፡፡ በምዕራፍ 9 እናቲቱ የሚለው ምንባብ ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ይበዛበታል የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

መ3. እና መ6. አብዛኛዎቹ ምንባቦች ላይ ነጠላ አረፍተ ነገሮች በዝተው ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ ሳይንስና ቴክኖሎጅ የሚለው ምንባብ ብዙ ነጠላ አረፍተ ነገሮች አሉት፡፡

መ4. ይህ ጉዳይ በደንብ ጊዜ ወስዶ መፈተሽ ያለበት ይመስለኛል፡፡ በቅድሚያ አንድን ምንባብ ብቻ ወስደን ብናይ በጥቅሉ ስንት አረፍተ ነገሮች እንዳሉት ከታወቀ በኋላ ስንቶቹ ነጠላና ውስብስብ እንደሆኑ ማጤን ይቻላል የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

መ5. ይህ በጥልቀት ተቆጥሮ ቢታይ ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ በምዕራፍ1 ያለው ምንባብ የነጠላ አረፍተ ነገሮቹ ቁጥር ከውስብስብ አረፍተ ነገሮቹ ይበልጣል የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

ቀን 13/10/17 ዓም

የትምህርት ቤቱ ስም ወልዋሎ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

ስዓት 2፡00-3፡10

7.በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ያሉ ምንባቦች በደንብ የተደራጁ፣ የሃሳብ ተያያዥነትና ግልፅነት ያላቸው ሃሳቦችን የያዙ ናቸው ምሳሌ ቢጠቅሱ

መ1. በእኔ እተያየት ሁሉም ምንባቦች የሃሳብ ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች አቅርበዋል፡፡ ለምሳሌ ባህላዊ ሽምግልና የሚለው ምንባብ ስለባህላዊ ሽምግልና ምንነት፣ ፋይዳ፣ የሚፈታቸው ጉዳዮችና የሽምግልና ሂደቶችን ሃሳባቸው ተያይዞ የቀረበበት ምንባብ ነው፡፡ በሃሳብ ቀላልነት ደረጃም በምዕራፍ1.2 እና 5 ያሉት ምንባቦች ቀላል ናቸው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

መ2. ግልፅ ሃሳብ የያዙ በርካታ ምንባቦች በመፅሃፉ ውስጥ አሉ፡፡ ለምሳሌ ሳይንስና ቴክኖሎጅ የሚለው ምንባብ አሻሚ ሃሳብ የለውም፡፡ ስለየአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች፣ ስለየተራቆተን አካባቢ ማልማት የሚዳሱት ምንባቦች ቀላል ሃሳብ የያዙ ናቸው፡፡

በአንፃሩ ደግሞ ስለባህል የሚያወራው ተበቺሳ የሚለው ምንባብ ለመረዳት የሚያስቸግር ይመስለኛል፡፡

መ3. እና መ.4 ሁሉም ምንባቦች የሃሳብ ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች አቅርበዋል፡፡ ነገር ግን እኩል ስፋትና ጥበት ባይኖራቸውም የሚያቀርቡ ሃሳብ ቀላልና ግልፅ ናቸው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

መ5. እና መ6. አብዛኛዎቹ ምንባቦች ቀላልና ግልፅ ሃሳብ የሚያቀርቡ ቢሆንም እናቲቱ የሚለው ልቦለድ ግን ከባድ ሃሳብ ይዟል የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡